የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፹፮
አዲስ አበባ–ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ/ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 86
ADDIS ABABA 24th July 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ዓ·ም
የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር
አዋጅ ...................................................... ገጽ ፪ሺ፫፻፵

## CONTENTS

Proclamation No. 361/2003
Addis Ababa City Government Revised Charter
Proclamation ........................................ Page 2340

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭
## የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ርዕሰ ከተማ እና የአፍሪካ ህብረትና የተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ተቋማት መቀመጫ በመሆኑ እንዲሁም የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ጥንቅር የሚያንፀባርቅ ሰፊና አዳጊ ነዋሪ ያለበት በመሆኑ በዘመናዊነቱ ደረጃውን የጠበቀ መልካም የሥራና የመኖሪያ ከተማ መሆን እንዳለበት በማመን፣

የአዲስ አበባ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን እንዳለውና ዝርዝሩ በሕግ እንደሚወሰን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የተደነገገውን መሠረት በማድረግ፣

የከተማው ነዋሪ ለከተማው ዕድገት ያለውን በጎ ምኞትና ታታሪነት በማጤንና ከተማው ያለውን የልማት አቅም በመመርኮዝ የዕድገት ዓላማውን በይበልጥ ለማሣካት የሚያስችለውን ሁኔታ ማመቻቸት በማስፈለጉ፣

ከተማው ኢንቬስትመንትን በመሳብ ለነዋሪው የኑሮ መሻሻልና ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት በር ከፋች በመሆን ተጨባጭ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል በመገንዘብ፣ የከተማው ተወዳዳሪነትና የልማት ቀጣይነት እውን እንዲሆን የከተማው አሠራርና አካሄድ ሥሉጥ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ እንዲሆንና ለውጥ አምጭና አስተናጋጅ በመሆን ከተማው ራሱን በራሱ እያደሰ ከጊዜው ጋር እንዲሄድ ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

## PROCLAMATION NO. 361/2003
## THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REVISED CHARTER PROCLAMATION

WHEREAS, it is believed that Addis Ababa must become a suitable urban space for work and residence measurable by modern standards in view of the fact that it is the capital of the Government of the Federal Democrtic Republic of Ethiopia and the seat of the African Union and of a variety of international organizations as well as it is a reflection of a large and growing residents representatives of Nations, Nationalities and Peoples;

WHREAS, the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia stipulates that the residents of Addis Ababa have full power of self-government and that the details thereof shall be setout by law;

WHWEREAS, it is necessary to create conditions which enable the city to maximize the achievements of its development objectives by giving due account to the best wishes and diligence of its residents and by relying on its development potentials;

WHEREAS, in order that the competitiveness and developmental continuity of the city become real and being aware that the city can, by attracting investment, have substantial contribution to the improvement of the lives of its residents and to the opening up of a way for the economic development of the country, it is found necessary to enable the city cope with time through self-renwal so that its operations and processes become efficient, effective and equitable as well as change-generative, and, receptive;

ያንዱ ዋጋ 6.00
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፹፱ አፈጻጸም የተገኙትን ተሞክሮዎች በማጤንና የአዲስ አበባ ከተማን አደረጃጀትና አመራር ከዲሞክራሲ መርሆዎችና ከመልካም የአስተዳደር ሥርዓት እንዲሁም ከወቅታዊ የዕድገትና የልማት አቅጣጫ ጋር በሚጣጣም መልኩ በማየት የተሻሻለ ቻርተር ማውጣት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፱/፪/እና አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ቻርተር ውስጥ፣

፩· "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪· "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫· "ከንቲባ" ማለት የከተማውን አስተዳደር የሚመራ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነው፤

፬· "የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት" ማለት የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ የመንገድ ሥራ አገልግሎት፣ የእሳትና ድንገተኛ አደጋ አገልግሎት፣ የክብር መዝገብ ሥራዎችን ጨምሮ የነዋሪዎች የእለት ተዕለት አገልግሎት፣ የመሬት ልማት እና አስተዳደር አገልግሎት፣ የከተማ ጽዳትና ውበት አገልግሎት እና የከተማው አስተዳደር የሚወስናቸውን ሌሎች አገልግሎቶች ይጨምራል፤

፭· "ክፍለ ከተማ" ማለት የከተማው ሁለተኛው ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤

፮· "ቀበሌ" ማለት የከተማው ሦስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን የሆነ የክፍለ ከተማ አካል ነው፤

፯· "የሥራ ሁኔታ" ማለት የከተማው አስተዳደር ከሥራ ኃላፊዎቹና ከሠራተኞቹ ጋር ያለውን ጠቅላላ ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን ይህም የሥራ ሰዓትን፣ ደመወዝን፣ ፈቃዶችን፣ ከሥራ በሚሰናበትበት ጊዜ የሚገባውን ክፍያ/ካለ/፣ የጤንነት እና ደህንነት፣ በሥራ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ስለሚከፈል ካሣ፣ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቶችንና የመሣሠሉትን ያጠቃልላል።

፫· ሕጋዊ ሰውነት

የከተማው አስተዳደር ሕጋዊ ሰውነት አለው።

፬· ስም

የከተማው ስም አዲስ አበባ ነው።

፭· ወሰን

አሁን ያለው የከተማው ክልል እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከተማው ወሰን የከተማው አስተዳደር ከኦሮሚያ ክልል ጋር በሚያደርገው ስምምነት ወይም በፌዴራል መንግሥት ይወሰናል፣ የወሰን ምልክትም ይደረግበታል።

፮· የሥራ ቋንቋ

የከተማው አስተዳደር የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው።

WHEREAS, it is found necessary to revise the Addis Ababa City Government Charter Proclamation No. 87/1997 by taking into account experiences gained in its application and by looking into the organization and management of the city from the prespective of democratic principles and good governance as well as contemporary trends of growth and development;

NOW, THEREFORE, in accordance with the provisions of Articles 49(2) and 55(1) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## *General Provisions*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003."

2. *Definitions*

Unless the context indicates otherwise, in this Charter:

1) "City" means the Addis Ababa City;
2) "City Government" means the Addis Ababa City Government;
3) "Mayor" means the chief executive officer of the City Government;
4) "Municipal Service" means water and sewerage service, road construction service, fire and emergency service, day to day services for residents including civil status record operations, land development and management, city sanitation and beatification and other services to be designated as such by the City Government;
5) "Sub-City" means a second administrative stratum of the City;
6) "Kebele" means a third administrative stratum of the City but a unit of a sub-City;
7) "Conditions of work" means the entire relations between the City Goverment and its officials and employees and shall include hours of work, salary, leaves, payments due to dissmissal, if any, health and safety, compensation to victims of employment injury,grievance procedure and other similar matters.

3. *Legal Personality*

The City Goverment shall have legal personality.

4. *Name*

The name of the City is Addis Ababa.

5. *Boundary*

Without prejudice to the existing one, the boundary of the City shall be delimited by an agreement to be made between the City Government and Oromia Regional Government or pursuant to the decision of the Federal Government.

6. *Working Language*

The working Language of the City Government is Amharic.

፯. የነዋሪዎች መብት

፩. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመ ንግሥት እና በሌሎች የሀገሪቱ ሕጐች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ነዋሪዎች ስለከተማው የሚወሰኑ ጉዳዮችን በሚመለከት መረጃ የማግኘት ፣ ሃሳብና ጥያቄ የማቅረብ እና መልስ የማግኘት መብት አላቸው።

፪. ነዋሪዎች የከተማው አስተዳደር የሚሰጠውን አገል ግሎት በእኩልነት፣ በግልጽነትና በፍትሐዊነት መርህ መሠረት የማግኘት መብት አላቸው።

፫. የከተማው አስተዳደር ፖሊሲ፣ በጀት፣ የሥራ ዕቅድና መመሪያ ለነዋሪዎች ይፋ መሆን አለበት።

፰. ስለምርጫ

በዚህ ቻርተር መሠረት የሚከናወኑ የከተማው ምርጫዎች በሀገሪቱ የምርጫ ሕግ መሠረት ይከናወናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የከተማው አስተዳደር ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር

፱. ዓላማ

የከተማው አስተዳደር የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

፩. ብቁ፣ ግልፅና ለነዋሪው ተጠያቂነት ያለበት መልካም የአስተዳደር ሥርዓት፣ ቀልጣፋና ፍትሐዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት እንዲሁም አስተማማኝ ፀጥታና ማህበራዊ ትስስር የተረጋገጠበት ከተማ የማድረግ፤

፪. የፌዴራል መንግሥት ርዕሰ ከተማ፣ ለአፍሪካ ህብረትና ለተለያዩ ዓለማቀፍ አህጉራዊ ድርጅቶች መቀመጫ የመሆን ሚናውን የማሳደግ፤

፫. አመቺ የመኖሪያ የሥራ ሁኔታ የመፍጠር እንዲሁም ነዋሪዎች የከተማውን ሁለገብ እንቅስቃሴ የሚወስኑበ ትንና የልማት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ የማመ ቻቸት፤

፬. የሀገሪቱ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በእኩልነት የሚኖሩበት፣ የባሕላቸው መግለጫ የሆነ ማዕከል እንዲሆን ማድረግ፤

፭. የነዋሪዎች ደህንነትና ምቾት የተጠበቀበት በተለይም ሕፃናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ሌሎች የተጐዱ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተለየ ድጋፍ የሚያገ ኙበት ከተማ የማድረግ፤

፮. ኢንቨስትመንትና ምርምርን በማበረታታትና በማጎ ልበት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የማምጣት፤

፯. ከተማውን የሀገሪቱ የንግድና የኢንዱስትሪ ማዕከል እንዲሆን የማድረግ፤ እና

፰. የአካባቢ ብክለትን በመከላከል የተፈጥሮ ሚዛኑን የጠበቀ ጽዱ፣ አረንጓዴና ምቹ ከተማ የማድረግ።

፲. የከተማው አስተዳደር የሥልጣን አካላት አደረጃጀት

፩. የከተማው አስተዳደር የሥልጣን አካላት የሚከተሉት ናቸው፣
  ሀ) የከተማው ምክር ቤት፤
  ለ) ከንቲባ፤
  ሐ) የከተማው ካቢኔ፤
  መ) የከተማው የዳኝነት አካላት፣ እና
  ሠ) የከተማው ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት።

፪. የክፍለ ከተማ የሥልጣን አካላት የሚከተሉት ናቸው፣
  ሀ) የክፍለ ከተማው ምክር ቤት፣
  ለ) የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ እና
  ሐ) የክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ፤

፫. የቀበሌ የሥልጣን አካላት የሚከተሉት ናችው።
  ሀ) የቀበሌ ምክር ቤት፣
  ለ) የቀበሌ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣
  ሐ) የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ፤ እና
  መ) የቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤት።

7. Rights of Residents

1) Without prejudice to the constitutions of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and other laws of the country, the residents of the City have the right to seek and receive information, forward their opinions, raise questions, and receive repiles concerning decisions relating to the City.
2) Residents have the right to get services to be rendered by the City Government in accordance with the principles of equality, transparency and equity.
3) Policies, budgets, plans and directives of the City Government must be publicized to residents.

8. *Election*

Elections for the Councils at all levels of the City Government, held pursuant to this Charter, shall be conducted in accordance with the electoral law of the country.

## PART TWO

## *Objectives, Organization, Powers and Functions of the city Government*

9. *Objectives*

The City Government shall have the objectives to:

1) maintain good governance in which effectiveness, transparancy and accountability, to the residents, prevail; make the City one in which expedient and equitable municipal services and reliable security and social harmony are ensured;
2) enlarge the role of the City as a capital city of the Federal Government and as a seat of the African Union and different intrrnational and regional organizations;
3) create favourable condtions of living and work as wellas to facilitate conditions in which residents determine the overall operations of the City and become beneficiaries of its development;
4) make the City a centre where Ethiopian Nations, Nationalities and Peoples reside in equality and express their cultures;
5) make the City a place where the well-being and comfort of residents are safely kept and particularly where children, women, the disabled, the elderly and other disadvataged segments of society avail themselves of special support;
6) bring about the city's speedy economic development through the encouragement and enhancement of investment and research;
7) make the City a centre of commerce and industry of the country;
and
8) make the City a naturally balanced, clean, green and favourable spot through the prevention of environmental pollution.

10. *Structure of the City Government Organs of Power*

1) The City Government Organs of Power are the following:
   (a) City Council;
   (b) Mayor;
   (c) City Cabinet;
   (d) City Judicial Organs; and
   (e) Office of the City Chief Auditor.
2) Sub-City Organs of Power are the following:
   (a) Sub-City Council;
   (b) Sub-City Chief Executive; and
   (c) Sub-City Standing Committee.
3) Kebele Organs of Power are the following:
   (a) Kebele Council;
   (b) Kebele Chief Executive;
   (c) Kebele Standing Committee; and
   (d) Kebele Social Courts.

፲፩· የከተማው አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

፩· የከተማው አስተዳደር በዚህ ቻርተር ተለይተው በተሰጡት ጉዳዮች ላይ የሕግ አውጪነትና የዳኝነት ሥልጣን እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባራት ዝርዝር ተለይተው ባልተካተቱ ጉዳዮች ላይ የሕግ አስፈጻሚነት ሥልጣን ይኖረዋል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከተማው አስተዳደር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ) የከተማውን ልማት የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን የማውጣትና በሥራ ላይ የማዋል፤

ለ) የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት ዕቅዶችን ማጽደቅ፣ በሥራ ላይ የማዋል፤

ሐ) የከተማውን አስተዳደር ሠራተኞች እና ኃላፊዎች እንዲሁም በዚህ ቻርተር የተገለጹትን የሥልጣን አካላት ባልደረቦች የሥራ ሁኔታ የመወሰን፤

መ) የከተማውን አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን የማቋቋም እንዲሁም የከተማውን የልማት ድርጅቶች ሕጋዊ አካል አድርጎ በእራሱ ወይም ከግሉ ዘርፍ ወይም ከሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ጋር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በሽርክና የማቋቋም፤

ሠ) ክፍለ ከተማዎችንና ቀበሌዎችን የማቋቋም፣ ወሰናቸውን የመወሰን እንዲሁም ለክፍለ ከተማዎች የበጀት ድጎማን የመመደብ፤

ረ) በከተማ፣ በክፍለ ከተማና በቀበሌ ደረጃ የሚሰጡ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ለይቶ መወሰንና የማደራጀት፣ የተለያዩ የማዘጋጃ ቤት የአገልግሎት መስጫ አማራጮችን በመጠቀምና ነዋሪውን በማሳተፍ ስሉጥ፣ ወጪ ቆጣቢና ፍትሐዊ አገልግሎት ማቅረብ፤ ደረጃውን የጠበቀና ተቀባይነት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መኖሩን የማረጋገጥ፤

ሰ) በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት በሕግ መሠረት የማስተዳደር፤

ሸ) የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፯/፲፱፻፷፯ መሠረት የተወረሱና የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች፣ የሠራቸውን ወይም በሕጋዊ መንገድ ያገኛቸውን ሌሎች ቤቶች የማስተዳደር ፣ የማልማት ወይም የመሸጥ ፣

ቀ) ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ የሆነ የግል ንብረትንና የቦታ ይዞታን በሕግ መሠረት ተመጣጣኝ ካሣ በመክፈል የማስለቀቅና የመውሰድ ፤

በ) የከተማውን በጀት የማዘጋጀት ፣ የማጽደቅና የማስተዳደር ፣ በዚህ ቻርተር ተለይተው በተሰጡት የገቢ ምንጮች ክልል ግብር፣ ቀረጥ እና የአገልግሎት ክፍያ በሕግ መሠረት የመወሰን፤ የመሰብሰብ፤ ፍሬግብርንና የተጣሉ ቅጣቶችን በሕግ አግባብ የማንሳት፣ በገቢ ማስገኛ ተግባራት የመሳተፍ እና ዕርዳታና ስጦታ የመቀበል፤

ተ) በፌዴራል መንግሥት በማስፈቀድ ከሀገር ውስጥ ምንጮች መበደርና ከሀገር ውጭ ያሉ የብድር ምንጮችን በማፈላለግ የፌዴራል መንግሥት እንዲበደርለት መጠየቅ፤ እና

ቸ) ከፌዴራል መንግሥት እና ከክልል አካላትና ተቋማት፣ ከግሉ ዘርፍ፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት ፈቃድ ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶችን መመሥረትና የትብብር ስምምነቶችን የማድረግ።

11. *Powers and Functions of the City Government*

1) The City Government shall have the power to make laws and exercise judicial powers specifically conferred on it by this Charter as well as executive powers and functions over matters that have not sepcifically been included in the details of the powers and functions of the executive organs of the Federal Government.

2) Without prejudice to the general provisions set forth under Sub-Article (1) of this Article, the City Government shal have the powers and functions to:

(a) issue and implement policies concerning the development of the City;

(b) approve and implement economic and social development plans;

(c) determine the administration and working conditions of employees and officials of the City Government as well as of the staff of other organs of power specified under this Charter;

(d) constitute the executive bodies of the City Government and to establish public enterprises, as legal entities, on its own or in partnership, as per applicable laws, with the private sector or other third parties;

(e) organize Sub-Cities and Kebeles, demarcate their borders and allocate budgetary subsidy to same;

(f) identify, determine and organize municipal services to be delivered at the level of the City, a sub-City and a Kebele; to provide efficient, effective and equitable services through the use of a variety of service delivery alternatives and the participation of the people and to ensure that a standasized, acceptable system of service delivery is in place;

(g) administer, according to law, the land and the natural resources located within the bounds of the City;

(h) administer, develop or sale the houses nationalized as per Government Ownership of Urban Lands and Extra Houses Proclamation No. 47/1975 and administered by the City Government as well as other houses which the City Government built or otherwise obtained lawfully;

(i) expropriate private property and/or clear and takeover land holdings designated as an object of public interest, subject to payment of commensurate compensation in accordance with the law;

(j) prepare, approve and administer the budget of the City; to determine and collect, according to law, taxes, duties and service charges out of the sources of income specifically given hereby to the City Government; to revoke taxes and penalties imposed as per the law; to participate in income-generating activities and to receive donations and gifts;

(k) borrow money from domestic sources under authorization by the Federal Government; to identify external sources of loan and request the Federal Government to borrow money on its behalf; and

(l) establish relations and conclude co-operation agreements with Federal and Regional Government organs and institutions, the private sector, nongovernmental organizations and, under authorization by the Federal Government, with various international organizations.

## ክፍል ሦስት
## ስለከተማው ምክር ቤት

### ፲፪· ስለምክር ቤት አባላት

፩· የምክር ቤቱ አባላት በየአምስት ዓመቱ በከተማው ነዋሪ ይመረጣሉ።

፪· የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር በምርጫ ሕግ መሠረት ይወሰናል።

፫· ማንኛውም የምክር ቤት አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት አይከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም።

፬· ማንኛውም የምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀልም አይከሰስም።

፭· የምክር ቤቱ አባላት ነፃ ናቸው። ተጠያቂነታቸውም፣

ሀ) ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፤

ለ) ለዚህ ቻርተር፤

ሐ) ለህሊናቸው፤ እና

መ) ለከተማው ነዋሪ ብቻ ይሆናል።

፮· ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ነዋሪ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል።

፯· ማንኛውም የምክር ቤት አባል በተመረጠበት ምክር ቤት የሥራ ዘመን በፈቃዱ ካልለቀቀ ወይም ካልተሰናበተ በስተቀር በምርጫ ቦርድ በሚከናወኑ ሌሎች ምርጫዎች ሊወዳደር አይችልም።

፰· ማንኛውም የምክር ቤት አባል የግል ጥቅሙና የከተማው ጥቅም የሚጋጩበት ሁኔታ ሲኖር ውሳኔ ከመስጠት መገለል እና ለምክር ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

### ፲፫· የከተማውን የሕግ አስፈፃሚ አካል ስለማደራጀት

በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያለው የፖለቲካ ድርጅት ወይም አብላጫ መቀመጫ ያለው የፖለቲካ ድርጅት ከሌለ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራ የከተማውን የሕግ አስፈፃሚ አካል ያደራጃል (ይመራል)።

### ፲፬· የከተማው ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

፩· ለከተማው አስተዳደር የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ለማዋል የከተማው ምክር ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ አዋጅ የማውጣት ሥልጣን አለው።

ሀ) የከተማውን አስፈፃሚ አካላት ለማቋቋም፣

ለ) የከተማውን አስተዳደር በጀት ለማጽደቅ፣

ሐ) የከተማውን መሪ ፕላን ለማውጣት፣

መ) በዚህ ቻርተር በተደነገገው መሠረት የከተማውን የዳኝነት አካላት ለማቋቋምና እንደየአግባቡ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን፣

ሠ) በዚህ ቻርተር መሠረት በከተማው አስተዳደር ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ ግብር እና ቀረጥ ለመጣል፣ የአገልግሎት ክፍያ ለመወሰን፣ እና

ረ) በከተማው አስተዳደር የወጡ ነባር ሕጎችን ለመተካት።

## PART THREE
## The City Council

### 12. *Members of the City Council*

1) Members of the Council shall be elected by residents of the City for a term of five years.

2) The number of members of the Council shall be determined according to the electoral law.

3) No member of the Council may be prosecuted on account of any vote he casts or opinion he expresses in the Council, nor shall any administrative action be taken against him.

4) No member of the Council may be arrested or prosecuted without the authorization of the Council, except in the case of *flagrante delicto* for a serious offence.

5. Members of the Council are free and their accountability shall be only to:

(a) the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

(b) this charter;

(c) their conscience; and

(d) the residents of the City.

6. Any member of the Council may, in accordance with the law, be discharged from his membership of the Council where the electorate has lost confidence in him.

7. No member of the Council shall be a candidate in other elections conducted by the National Electoral Board, pending the term of office of the Council he is elected to, unless he has resigned or has been discharged from membership of the council.

8. Where there exists a conflict of interest of the City and of any member of the Council, such a member shall so notify the Council and refrain from rendering of decision. The details thereof shall be set out by Regulations.

### 13. Formation of the Executive Organ of the City

The political party occupying the majority of seats of the Council or, where such does not exist, the coalition of political parties shall form, and give leadership to, the executive organ of the City.

### 14. *Powers and Functions of the City Council*

1) So as to realize the powers and functions entrusted to the City government, the city Council shall have power to promulgate Proclamations on the following matters:

(a) to constitute the executive organs of the City.

(b) to approve the budget of the City Government;

(c) to issue the Master plan of the City;

(d) to establish the judicial bodies of the City and to determine, as the case may be, their powers and functions, in accordance with the provisions of this Charter;

(e) to levy taxes and duties as well as set service charges upon financial matters falling under the power of the City Government in accordance with this Charter; and

(f) to replace existing laws issued by the City Government.

፪. የከተማው ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ) በሥልጣኑ ክልል ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ ከተማ አቀፍ ፖሊሲ ያወጣል፤

ለ) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጡ አዋጆች ላይ ሥልጣን ሊሰጠው ደንብ ያወጣል፤

ሐ) የከተማውን የአጭርና የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዕቅድ እና ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፤

መ) በዚህ ቻርተር ተለይተው በተመለከቱት የገቢ ምንጮች ላይ ግብር እና ቀረጥ ይጥላል፣ የአገልግሎት ክፍያ ይወስናል፤

ሠ) የምክር ቤቱን አፈጉባዔ፣ ምክትል አፈጉባዔና ፀሐፊ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመርጣል እንዲሁም የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ያቋቁማል፤

ረ. የከተማውን ከንቲባና ምክትል ከንቲባ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመርጣል፤

ሰ) በከንቲባው አቅራቢነት የከተማውን ካቢኔ አባላት ሹመት ያፀድቃል፤

ሸ) የከተማውን ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ዳኞች እንዲሁም የዋናው ኦዲተር ሹመት ያፀድቃል። የዳኞች አስተዳደር ጉባዔን ያቋቁማል፣ አባላቱንም ይሠይማል፤

ቀ) ተጠሪነታቸው ለእርሱ የሆኑ የአስተዳደራዊ የመዳኘት ሥልጣን የተሠጣቸው ሌሎች አካላት ፕሬዚዳንቶችን እንዲሁም በሕግ መሠረት ሹመታቸው በምክር ቤቱ መጽደቅ ያለበትን ሌሎች ባለሥልጣናት ሹመት ያፀድቃል፤

በ) የከተማውን አስፈጻሚ አካላትና የልማት ድርጅ ቶችን ያቋቁማል፤

ተ) የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ያቋቁማል፣ አባላቱንም ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ይሰይማል፤

ቸ) በማንኛውም ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከንቲባው ከሚያቀርባቸው ሦስት እጩዎች መካከል ምክር ቤቱ የውጭ ኦዲተር ይሠይማል፣ የውጭ ኦዲተሩ የሚያቀርበውን ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

ኀ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን የጥራት ደረጃ እና የአገልግሎት ክፍያ ያፀድቃል፤

ነ) የክፍለ ከተማና የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ብዛት ይወስናል፤

ኘ) በሚያወጣው ቀመር መሠረት የክፍለ ከተማዎችን የበጀት ድጎማ ይመድባል፤

አ) ከከንቲባው ወይም ተጠሪነታቸው ለእርሱ ከሆኑ አካላት የሚቀርቡለትን ወቅታዊ ሪፖርቶች መርምሮ ውሣኔ ይሠጣል፤

ከ) በፌዴራል መንግሥት በተፈቀደው መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች ጋር የሚደረጉ የብድር ስምምነ ቶችን መርምሮ ያፀድቃል፤

ኸ) ለምክር ቤቱ አባላት የሥነ ምግባር ደንብ ያወጣል፤

ወ) የከተማው ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ፣ የምክር ቤቱ አፈጉባዔ፣ ምክትል አፈጉባዔ፣ የከተማው ካቢኔ አባላት፣ ዋና ኦዲተር እንዲሁም ሌሎች የምክር ቤት አባላት የሥነ ምግባር ጉድለት ፈፅመዋል በሚባ ልበት ጊዜ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ምርመራ ያደርጋል፣ ምሥክሮች ይሠማል፣ ሌላ ማስረጃ እንዲ ቀርብ ያደርጋል፣ ውሣኔም ይሰጣል።

2) The City Council shall have the powers and functions to:

(a) adopt policies on matters falling within the purview of its power;

(b) issue Regulations pursuant to powers vested in it by Proclamations enacted by the House of Peoples' Representatives;

(c) approve the short-term and long-term economic and social development plans and annual budgets of the City;

(d) levy taxes and duties and set service charges on revenue sources specifiied under this Charter;

(e) elect from among its members, the Spokesperson, Deputy Spokesperson and Secretary of the Council and establish the Secretariat of the Council;

(f) elect, from among its members, the City Mayor and Deputy Mayor;

(g) approve the appointment of members of the City Cabinet upon the recommendation of the Mayor;

(h) approve, the appointment of the President, Vice President and judges of the City Courts and of the Chief Auditor; as well as to establish the Judicial Administration Commission and to designate its members;

(i) approve, the appointment of presidents of bodies accountable to it and having semi-judicial powers and of other officials whose appointment has to be approved by it as per the law;

(j) establish the executive organs and public enterprises of the City;

(k) establish the committees of the Council and designate their respective members from among its members;

(l) designate an external auditor from among three candidates to be proposed by the Mayor at any time it is so required, and to examine and render decision upon the report submitted by the external auditor;

(m) approve the quality standard of and charges for municipal services;

(n) determine the number of members of Sub-City and Kebele Councils;

(o) allocate budgetary subsidy to Sub-Cities according to the formula it adopts;

(p) examine and decide upon periodic reports submitted by the Mayor or by organs accountable to it;

(q) approve loan agreements made with domestic sources as per the authorization of the Federal Government;

(r) issue the Code of Conduct for members of the Council;

(s) conduct investigation, hear witnesses, cause other evidence to be produced and render decision, according to Regulations to be issued, where it is alleged that the Mayor, Deputy Mayor, the Council's Spokesperson and Deputy Spokesperson, the City's Cabinet members, the Chief Auditor or other members of the Council have committed breach of discipline.

**፲፭. የከተማው ምክር ቤት የሥራ ዘመን እና የስብሰባ ሥነ ሥርዓት**

፩. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። ምክር ቤቱ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይኖረዋል፣ መደበኛ ስብሰባው በየሁለት ወሩ ይሆናል።

፪. በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ከአባላቱ ጠቅላላ ቁጥር ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል።

፫. በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ውሣኔ ሊተላለፍ የሚችለው በስብሰባው ላይ የተገኙት አባላት ከግማሽ በላይ ሲደግፉት ነው።

፬. ለከተማው ፀጥታ ወይም ደህንነት ወይም የግለሰቦችን ወይም የሕጋዊ አካላትን ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር የምክር ቤቱ ስብሰባ ለሕዝብ ክፍት ይሆናል።

፭. የምክር ቤቱ አፈጉባዔ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤ የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈጉባዔው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

፮. ምክር ቤቱ ስለአሠራሩ የሚወስን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል።

**፲፮. የከተማው ምክር ቤት መዝገብ አያያዝ**

ምክር ቤቱ አሠራሩን እና ውሣኔውን የሚመዘግብበት መዝገብ ይኖረዋል፣ለከተማው ፀጥታ ወይም ደህንነት ወይም የግለሰቦችን ወይም የሌሎችን መብት ይጋፋል ተብሎ በምክር ቤቱ ካልተወሰነ በስተቀር መዝገቡ ለሕዝብ ግልጽ ይሆናል።

**፲፯. ስለ ምክር ቤቱ ተጠሪነትና መበተን**

፩. የከተማው ምክር ቤት ተጠሪነት ለፌዴራል መንግሥትና ለከተማው ነዋሪዎች ይሆናል።

፪. የከተማው ምክር ቤት ሊበተን የሚችለው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በእራሱ ውሣኔ ይሆናል። በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፷፩ ንኡስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ) የከተማው ምክር ቤት የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በራሱ ውሳኔ ሊበተን ይችላል።

ለ) በጣምራ አስፈፃሚነት ሥልጣን የያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራነት ፈርሶ በምክር ቤቱ የነበራቸውን አብላጫነት ያጡ እንደሆነ የከተማው ካቢኔ ተበትኖ በምክር ቤቱ ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ ጣምራ ካቢኔ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመመሥረት እንዲቻል በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ይጋበዛል። የፖለቲካ ድርጅቶች አዲስ ካቢኔ ለመፍጠር ወይም የነበረውን ጣምራነት ለመቀጠል ካልቻሉ ምክር ቤቱ ይበተናል።

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ "ሀ" ወይም "ለ" መሠረት ምክር ቤቱ የተበተነ እንደሆነ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ መደረግ አለበት።

መ) ምርጫው በተጠናቀቀ በሠላሣ ቀናት ውስጥ አዲሱ የከተማው ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።

ሠ) የከተማው ምክርቤት ከተበተነ በኋላ ከተማውን የሚመራው ሥልጣን ይዞ የነበረው የሕግ አስፈፃሚ አካል የዕለት ተዕለት የአስፈፃሚነት ሥራ ከማከናወንና ምርጫ ከማካሔድ በስተቀር አዲስ ሕጎችን ማውጣት ወይም ነባር ሕጎችን መሻርና ማሻሻል አይችልም።

15. *Term of Office of the City Council and Its Meeting Procedures*

1) The term of office of the Council shall be five years. The council shall have regular and extraordinary meetings and the regular meeting shall be held every two months.
2) There shall be a quorum where more than half of members of the Council are present at its meetings.
3) A decision, in any meting of the Council, may be passed where more than half of the members in attendance second it.
4) The meetings of the Council shall be open to the public unless it is otherwise necessary for the city's security or safety or for the protection of the interest of individuals or juridical persons.
5) The Spokesperson of the Council may call an extraordinary meeting; he shall also call an extraordinary meeting where more than half of the members of the Council so demand.
6) The Council shall issue internal Regulations that determine its operations.

16. *Keeping of Records by the City Council*

The council shall have a register for its proceddings and decisions. The Register shall be public unless the Council decides otherwise in consideration of the security or safety of the City, or the rights of individuals and others.

17. *Accountability and Dissolution of the Council*

1) The City Council shall be accountable to the Federal Government and to the residents of the City.
2) The dissolution of the City Council may be effected by the House of Peoples' Representatives or by its own decision. Without prejudice to Article 61 (3) of this Charter:
   (a) the City Council may dissolve itself before the lapse of its term of office in order for a new election to be conducted.
   (b) where a coalition of political parties seizing executive power breaks up and fails to occupy the majority seats of the Council, the Cabinet shall be dissolved, and the political parties in the Council shall be invited by the Ministry of Federal Affairs to form a coalition Cabinet within a week. If the political parties fail to form a new Cabinet or to continue the coalition, however, the City Council shall be dissolved.
   (c) new election shall be held within six months if the City Council is dissolved pursuant to sub-Article (2) (a) or (b) of this Article.
   (d) the new City Council shall commence work within thirty days after the conclusion of the election.
   (e) the executive organ in power, following the dissolution of the City Council, may not make, amend or repeal laws but only carry out day-to–day executive functions and undertake elections.

፲፰· የከተማው ምክር ቤት አፈጉባኤ

ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ አፈጉባኤው፣

፩· የሥራ ዘመኑ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፣ ሥራውን በፈቃዱ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነት ሲታገድ ወይም የምክር ቤት አባልነቱ ሲቋረጥ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፣ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፤

፪· የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ይመራል፤

፫· ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ምክር ቤቱን ይወክላል፤

፬· የምክር ቤቱን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፣ የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ያስተባብራል፤

፭· የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት በጀት ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

፮· የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

፯· ምክር ቤቱ ያፀደቃቸው ሕጎች በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ እንዲወጡ ያደርጋል፤

፰· ምክር ቤቱ በአባላት ላይ የሚወስዳቸውን የሥነ ሥርዓት እርምጃዎች ያስፈጽማል፤

፱· በምክር ቤት ስለሚወሰኑት ውሳኔዎች ወቅታዊ መግለጫ ለነዋሪዎች ይሰጣል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፣የምክር ቤቱ ሰነዶች ለነዋሪዎች ክፍት እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፲· የምክር ቤቱን አባላት የአቅም ግንባታ ሥራ እቅድ ያዘጋጃል፣ ከሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ጋር በመቀናጀት ያስፈጽማል፤

፲፩· ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር አቻ ምክር ቤቶች ጋር በመተባበር የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፤

፲፪· ከምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፲፱· የከተማው ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ

ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ አፈጉባኤ ሆኖ ምክትል አፈጉባኤ፣

፩· በአንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ለምክትል አፈጉባኤውም የሚሠራ ይሆናል፣

፪· አፈጉባኤው በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፣

፫· በአፈጉባኤው የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፳· የከተማው ምክር ቤት ፀሐፊ

ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ ሆኖ የምክር ቤቱ ፀሐፊ፣

፩· ከአፈ ጉባዔው ጋር በመመካከር የምክር ቤቱን አጀንዳ ያዘጋጃል ፣ የምክር ቤቱን ቃለ ጉባዔ ይይዛል ፣ ያትማል፤

፪· የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች ቃለ ጉባዔዎችና ሰነዶች እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል ፣ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ቃለ ጉባዔዎችን ያሠራጫል፤

፫· ሥራውን በራሱ ፈቃድ ሲለቅ ፣ በምክር ቤቱ ከኃላፊነቱ ሲታገድ ወይም የምክር ቤት አባልነቱን ሲያቋርጥ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፣ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፤

፬· በአፈ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

18. *Spokesperson of the City Council*

The Spokesperson, being accountable to the Council, shall:

1) have a term of office co-extensive with that of the Council provided that he may be removed from his post, prior to the end of such term, upon resignation, suspension from office or termination of his membership in the Council; details thereof shall be set out by internal regulations of the Council;
2) direct the Secretariat of the Council;
3) represent the Council in all its dealings with third parties;
4) call, and preside over, the meetings of the Council and co-ordinate the committees thereof;
5) prepare the budget of the Secretariat of the Council and implement same upon approval;
6) employ and administer the staff of the Secretariat of the Council in accordance with civil service laws;
7) ensure that laws adopted by the Council are published in the Addis Negarit gazette;
8) execute disciplinary decisions passed by the Council against its members;
9) give periodic briefings to residents on decisions passed by the Council and notify same to concerned organs, ensure that documents of the Council are made accessible to residents;
10) prepare plans for capacity building of members of the Council and implement same jointly with concerned executive bodies;
11) create cordial relations and exchange experiences with internal and external, counterpart councils;
12) perform other functions assigned to him by the Council.

19. *Deputy Spokesperson of the City Council*

The Deputy Spokesperson, being accountable to the Spokesperson of the Council, shall:

1) the provisions of Article 18(1) shall also be applicable in respect of the Deputy Spokesperson;
2) act on behalf of the Spokesperson in case of absence or incapacitation of the latter;
3) perform other functions assigned to him by the Spokesperson.

20. *Secretary of the City Council*

Being accountable to the Spokesperson of the Council, the Secretary of the Council:

1) shall prepare the agenda of the Council in consultation with the Spokesperson publish and keep the minutes of the Council;
2) shall ensure that the minutes and documents of the committees of the Council are recorded and kept; distribute minutes in accordance with the internal regulations of the Council;
3) may be removed from his post, prior to the end of his term of office, oupn resignation, suspension from office or termination of his membership in the Council; details thereof shall be set out by the internal regulations of the Council;
4) perform other functions assigned to him by the Spokesperson.

## ክፍል አራት
## የከተማው አስፈጻሚ አካላት

፳፩. ከንቲባ

፩. ተጠሪነቱ ለከተማው ምክር ቤትና ለፌዴራል መንግሥት ሆኖ ከንቲባው የከተማው አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከንቲባው

ሀ) በከተማው ምክር ቤት የሚወሰኑትን ውሣኔዎች፣ የሚወጡትን ሕጐች የሚፀድቁትን ዓመታዊ እቅድና በጀት ያስፈጽማል፤

ለ) የከተማው ልዩ ልዩ ፖሊሲ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት እቅድ፣ ዓመታዊ በጀት በካቢኔው ከተመከረበት በኋላ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

ሐ) የከተማው አምባሳደር በመሆን ከተማውን ይወክላል፤

መ) የከተማውን ህግና ሥርዓት ያስከብራል፤

ሠ) የካቢኔ አባላትን መርጦ ሹመታቸውን በምክር ቤቱ ያፀድቃል፣ ካቢኔውን ይመራል፤

ረ) የከተማው ምክር ቤት እንደአስፈላጊነቱ የውጭ ኦዲተር ለመሠየም ሲወስን ሦስት እጩ ኦዲተሮች ያቀርባል፤

ሰ) ካቢኔውን በማማከር ሙያዊ ብቃትን መሠረት በማድረግ የከተማውን ሥራ አስኪያጅ በተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ይቀጥራል፣ ያሠናብታል፤

ሸ) የነዋሪዎችን ቅሬታ ያስተናግዳል፤

ቀ) በብሔራዊና የሕዝብ በዓላት ሥነ ሥረዓቶች ከተማውን ይወክላል፤

በ) የከተማው ዕቅድ፣ በጀት፣ እንዲሁም የሥራ አፈጻጸም ለሕዝብ የሚቀርብበት እና አስተያየት የሚሰጥበት መድረክ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

ተ) ዓመታዊ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክር ቤቱ በሚወስነው መሠረት ወቅታዊ ሪፖርት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ እንዲሁም በዚህ ቻርተር አንቀፅ ፷፩ ንዑስ አንቀፅ ፮ በተገለፀው መሠረት ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል፤

ቸ) ደረጃውን የጠበቀ ፍትሐዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ኀ) ለከተማው የሚያስፈልገውን የድጋፍ መጠን በማዘጋጀት በከተማው ካቢኔ ከተመከረበት በኋላ ለፌዴራል መንግሥት ያቀርባል፤

ነ) የአዋጅ እና የደንብ ረቂቆችን በማዘጋጀት በካቢኔው ከተመከረበት በኋላ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

ኘ) ሹመታቸው በምክር ቤቱ መጽደቅ ያለበትን ሣይጨምር የከተማውን አስፈጻሚ አካላት የበላይ ኃላፊዎች ይሾማል። ለከተማው የልማት ድርጅቶችና ሌሎች አካላት የቦርድ ሰብሳቢዎችና አባላትን ይሰይማል፤

አ) የራሱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል፤

ከ) በህግ መሠረት ሽልማቶችን ይሠጣል፤

ኸ) በከተማው ምክር ቤት እና በፌዴራል መንግሥት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፫. የከንቲባው የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፣ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ፣ በምክር ቤቱ ከኃላፊነቱ ሲታገድ ወይም የምክር ቤት አባልነቱን ሲያቋርጥ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነት ሊሠናበት ይችላል፣ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

## PART FOUR
## EXECUTIVE BODIES OF THE CITY

21. Mayor

1) The Mayor, being accountable to the City Council and the Federal Government, shall be the Chief Executive Officer of the City.

2) Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Mayor shall:

(a) execute decisons, laws, annual plan and budget adopted by the City Council;

(b) propose, to the City Council, diverse policies, economic and social development plans and annual budget of the City, subsequent to consultation thereon by the Cabinet; ensure the implementation thereof upon approval;

(c) represent the City as an ambassador thereof;

(d) ensure the observance of law and order in the City;

(e) nominate Cabinet members of the City Council and have their appointment approved by the Council, as well as direct the Cabinet;

(f) propose three candidates where the City Council decides, as may be necessary, to appoint an external auditor;

(g) subject to consulation with the Cabinet and in consideration of professional competence, hire and fire the City Manager under a contract of employment for a definite period;

(h) handle the grievances of residents;

(i) represent the City at events of national and public holidays;

(j) cause to be organized forums where plans, budget and work performances of the City are presented to, and commented by, the public;

(k) submit annual and, as the Council may determine as necessary, periodic reports to the Council; submit reports to the Ministry of Federal Affairs pursuant to Article 61 (6) herin;

(l) ensuré that a standardized, equitable municipal service delivery is implemented;

(m) prepare and propose to the Federal Government the amount of support needed by the City, after consultation thereon by the City Cabinet;

(n) prepare and submit draft proclamations and regulations to the Council after consultation thereon by the Cabinet;

(o) appoint the heads of the executive bodies of the City, other than those whose appointment is approved by the council; designate Board Chairpersons and members for public enterprises and other organs of the City.

(p) organize his own Office;

(q) award prizes in accordnace with law;

(r) perform other functions assigned to him by the City Council and the Federal Government;

3) The term of office of the Mayor shall be that of the Council provided that he may be removed from his post, prior to the end of such term, upon resignation, suspension from office or termination of his membership in the Council; details thereof shall be set out by the internal regulations of the Council.

፳፪· ምክትል ከንቲባ

ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ ምክትል ከንቲባው፣

፩· ከንቲባው በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፤

፪· በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከና ውናል።

፫· በአንቀጽ ፳፩(፫) የተጠቀሰው ለምክትል ከንቲባውም የሚሠራ ይሆናል።

፳፫· የከተማው ካቢኔ

፩· ተጠሪነቱ ለከንቲባው እና በጋራ ለሚወስነው ውሣኔም ለከተማው ምክር ቤት ሆኖ የከተማው ካቢኔ፣

ሀ) በፌዴራል መንግሥትና በከተማው ምክር ቤት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ውሣኔዎችና ደረጃዎች መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) ምክር ቤቱ ያወጣቸው ፖሊሲዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) ከተማ አቀፍ ፖሊሲና የአዋጅና የደንብ ረቂቅ ያመነጫል፤

መ) በከተማው ዓመታዊ እቅድና በጀት ላይ ይመክራል፤

ሠ) የከተማውን አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት አደረ ጃጀት ይወስናል።

ረ) በምክር ቤቱ በሚወጡ አዋጆች ላይ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችን ያወጣል፤

ሰ) በከንቲባውና በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፪· የካቢኔው የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል።

፳፬· የከተማ ሥራ አስኪያጅ

፩· ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ የከተማው ሥራ አስኪያጅ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈጻሚ ነው።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከተማው ሥራ አስኪያጅ፤

ሀ) ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንዲቋቋሙ ወይም ሌሎች የአገልግሎት መስጫ አማራጮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ለከን ቲባው ሃሳብ ያቀርባል፤

ለ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ኃላፊዎች እንዲሾሙ ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሹመታቸው ሲፀድቅም ሥራቸውን በሕግ መሠረት ይመራል፣ ያሰናብታል፤

ሐ) ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅነት በተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣ ከክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጆች ዓመታዊና አስፈላጊ ሲሆን ወቅታዊ ሪፖርቶችን ይቀበላል፣ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

መ) ከተማ አቀፍና ክፍለ ከተማ ዘለል የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በመተለከተ እቅድ እና በጀት ለከን ቲባው ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ) የአገልግሎት አቅርቦት መለኪያዎች እና መመሪ ያዎች በማጠናከር ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደረጋል፤

ረ) ሥሉጥ፣ ግልፅና ፍትሐዊ የማዘጋጃ ቤት አገል ግሎት መሠጠቱን ያረጋግጣል፤

ሰ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከቱ ውሣኔ ዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

22. Deputy Mayor

The Deputy Mayor, being accountable to the Mayor, shall:

1) act on behalf of the Mayor in case of absence or incapacitation of the latter;
2) perform other functions assigned to him by the Mayor.
3) The provisions of Article 21(3) shall also be applicable in respect of the Deputy Mayor.

23. The City Cabinet

1) The City Cabinet, being accountable to the Mayor and, for its joint decisions, to the City Council, shall
   (a) ensure that proclamations, regulations, resolutions and standards adopted by the City Council and by the Federal Government are implemented;
   (b) ensure that policies adopted by the Council are implemented;
   (c) initiate city-wide policies as well as draft proclamations and regulations;
   (d) deliberate on the annual plan and budget of the City;
   (e) decide on the organizational structure of the executive bodies of the City Government;
   (f) issue Regulations pursuant to authority given to it by proclamations to be issued by the Council;
   (g) perofrm other functions assigned to it by the Mayor and the Council.

(2) The term of office of the Cabinet shall be that of the Council.

24. City Manager

1) The City Manager, being accountable to the Mayor, shall be the executive of municipal services.
2) Without prejudice to the generality of sub-Article (1) of this Article, the City Manager shall;
   (a) make recommendations, to the Mayor, for the establishement of municpal bodies accountable to himself or for the implementation of other service delivery alternatives;
   (b) nominate candidates for appointment, by the Mayor, as heads of municipal service bodies; direct, in accordance with law, the operations of such heads and effect their discharge;
   (c) hire, under a contract of employment for a definite period, competent professionals as sub-City Managers as well as administer and discharge same; receive, examine and decide upon annual and, where necessary, periodic reports from sub-City Managers;
   (d) submit to the Mayor action plans and budget proposals concerning city-wide and inter-sub-City municipal services and implement same upon approval;
   (e) develop and submit to the Mayor service delivery indicatiors and guidelines and implement same upon endorsement thereof;
   (f) ensure the delivery of efficient, transparent and equitable municipal services;
   (g) executie decisions concerning municipal services;

ሸ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከት የፖሊሲ ሃሳብ እና የህግ ረቂቅ በማመንጨት ለከንቲባው ያቀርባል፤

ቀ) የከተማው ምክትል ሥራ አስኪያጅ እንዲቀጠር ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ይቀጥራል፤

በ) የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፤

ተ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ የነዋሪዎችን አቤቱታ ያስተናግዳል፤ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በተቻለ ፍጥነት መልስ ይሠጣል፤

ቸ) በሥሩ ከሚሠሩ አካላት ኃላፊዎች የተውጣጣ የሥራ አመራር ኮሚቴ ያቋቁማል፤ ይመራል፤

ነ) በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፫· የከተማው ሥራ አስኪያጅ በከተማው ምክር ቤት ስብሰባዎች ያለድምፅ መሳተፍ ይችላል።

፳፭· ምክትል የከተማ ሥራ አስኪያጅ

ተጠሪነቱ ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ምክትል የከተማ ሥራ አስኪያጁ፣

፩· የከተማው ሥራ አስኪያጅ በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፤

፪· በከተማው ሥራ አስኪያጅ የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናወናል።

ክፍል አምስት
ሌሎች አስፈጻሚ አካላት

፳፮· የከተማው ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት

፩· የከተማውን አስተዳደር የሥልጠት፣ የክንዋኔ ብቃት፣ የሐብት አጠቃቀምና አስተዳደር በመቆጣጠር ለከተማው ምክር ቤት ሪፖርት የሚያቀርብ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ይኖራል።

፪· የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሥራውን የሚያከናውነው በነፃነት ነው።

፫· ዋናው ኦዲተር ቀጥሎ ካሉት ምክንያቶች ውጭ ያለፈቃዱ የጡረታ ዕድሜ ከመደረሱ በፊት ከሥራው አይነሣም፣

ሀ) የዲስፕሊን ጥፋት በመፈጸም ወይም በከባድ ችሎታ ማጣት ወይም ቅልጥፍና ማጣት፣

ለ) በሕመም ምክንያት ኃላፊነቱን ለመወጣት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም

ሐ) የከተማው አስተዳደር ምክር ቤት በአብላጫ ድምጽ ሲወስን።

፬· የከተማው ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በማዘጋጀት ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በጀቱን ያስተዳድራል።

፳፯· የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን

፩· በዋነኛነት ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና በውክልና ለከተማው አስተዳደር ተጠሪ የሆነ የከተማው ፖሊስ፣

ሀ) በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ መሠረት በሚወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይቋቋማል፤

ለ) ዕቅድና በጀቱን በማዘጋጀት ለከንቲባው ያቀርባል፣ በከተማ ምክር ቤት ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ዓመታዊና ወቅታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሪፖርቶቹም በከተማው ካቢኔና ምክር ቤት ተመርምረው ውሣኔ ይሰጥባቸዋል።

(h) initiate and submit to the Mayor policy proposals and draft laws concerning municipal services;

(i) recommend, to the Mayor, a candidate for employment as Deputy City Manager and hire same upon approval;

(j) submit work performance reports to the Mayor;

(k) recieve and handle as well as respond, reasonably fast, to the pleas of residents concerning municipal services;

(l) constitute and direct a management committee consisting of the heads of organs subordinated to him,

(m) perform other functions assigned to him by the Mayor.

3) The City Manager may participate, without a vote, in meetings of the City Council.

25. Deputy City Manager

The Deputy City Manager, being accountable to the City Manager, shall;

1) act on behalf of the City Manager in case of his absence or incapacitation;

2) perform other functions assigned to him by the City Manager.

PART FIVE
OTHER EXECUTIVE BODIES

26. Office of the City Government Chief Auditor

1) There shall be an Office of the Chief Auditor of the City Government to inspect and report to the City Council on the efficiency, performance effectiveness, resource utilization and administration thereof.

2) The Office of the Chief Auditor shall be independent in the performance of its functions.

3) The Chief Auditor shall not be removed from his office before retirement, except for resignation or one of the following reasons:

(a) disciplinary breach, grave incompetence or poor performance;

(b) proven inability to fulfil his responsiblities because of illness; or

(c) where the City Council decides by majority vote to that effect.

4) The Chief Auditor shall prepare and submit to the City Council the budget of his office and administer same upon approval.

27. Addis Ababa City Police Commission

1. The City Police Commission, being accountable primarly to the Federal Police Commission and, by delegation, to the City Government, shall:

(a) be established by Regulations of the Council of Ministers issued pursuant to the Federal Police Commission Proclamation;

(b) prepare and submit its plan and budget proposal to the Mayor and implement same upon approval by the City Council; submit annual and periodic performance reports, to the Mayor, for examination and decision by the City Cabinet and the City Council.

፪· የከተማው ፖሊስ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ይሾማሉ።

፫· የከተማውን ፖሊስ የዕለት ተዕለት ሥራ የመከታተል ኃላፊነት የከንቲባው ይሆናል።

፳፰· <u>የአዲስ አበባ ከተማ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት</u>

፩· የከተማው ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በከተማው ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ ክስ ይመሰርታል፣ ይከራከራል፣ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፪· የመሥሪያ ቤቱ አደረጃጀት በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕገ ይወሰናል።

፳፱· <u>የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን</u>

የከተማው አስተዳደር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ መሠረት የሚቋቋምና የሚሠራ የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ይኖረዋል።

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>ክፍለ ከተማና ቀበሌ</u>

፴· <u>ስለ ክፍለ ከተማ</u>

፩· ክፍለ ከተማዎች ባልተማከለ የሥልጣን ክፍፍል መርህ በተሰጠው የቦታ ክልል ማዘጋጃ ቤት በመሆንና ከከተማው ማዕከል ጋር በመቀናጀት ይሠራሉ።

፪· ክፍለ ከተማ በሥሩ የሚገኙትን ቀበሌዎች ያስተዳድራል።

፫· ክፍለ ከተማዎች በአካባቢያቸው ሕግና ሥርዓት የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው።

፬· የክፍለ ከተማ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።

፴፩· <u>ስለክፍለ ከተማና ቀበሌ ወሰን</u>

፩· የክፍለ ከተማዎችና የቀበሌዎች ወሰን በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማው ምክር ቤት ይወሰናል።

፪· የከተማው ምክር ቤት የነዋሪዎችን አስተያየት ፣ አመቺ የአገልግሎት አቅርቦት፣ የከተማ ልማት ዕቅድና የሕዝብ ብዛት መሠረት በማድረግ አዲስ ክፍለ ከተማ ወይም ቀበሌ ሊያቋቁም ወይም ያለውን ክፍለ ከተማ ወይም ቀበሌ እንደገና ሊያዋቅር ይችላል።

፴፪· <u>የክፍለ ከተማ ምክር ቤት</u>

፩· ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ነዋሪና ለከተማው ምክር ቤት ሆኖ የክፍለ ከተማው ምክር ቤት፣

ሀ) የክፍለ ከተማውን የኢኮኖሚ ፣ የማህበራዊ ልማት እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ዕቅድ ያፀድቃል፣

ለ) የምክር ቤቱን አፈ ጉባዔ ፣ ምክትል አፈጉባዔ እና ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል ይመርጣል፣

ሐ) የክፍለ ከተማውን ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አብላጫ የምክር ቤት መቀመጫ ባለው የፖለቲካ ድርጅት አቅራቢነት ከአባላቱ መካከል ይመርጣል፣

መ) በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቅራቢነት የክ ፍለ ከተማውን ቋሚ ኮሚቴ አባላትን ሹመት ያፀደቃል፣

ሠ) ከከተማው ምክር ቤት የሚመድብለትን በጀት ይደለድላል፣

ረ) የክፍለ ከተማውን ምክር ቤት ኮሚቴዎች ያቋቁማል፣

ሰ) ከክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ይቀበላል፣ መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፣

ሸ) የክፍለ ከተማው ምክር ቤት ስለ አሰራሩ የሚወስን ውስጠ ደንብ ያወጣል።

2) The City Police Commissioner and Deputy Commissioner shall be appointed by the Minister of Federal Affairs.

3) The responsibility to follow up the daily operations of the City Police Commission shall rest with the Mayor.

28. Public Prossecution Office of the City Government

1) The City Government Public Prosection Office shall prosecute such penal offences that fall under the jurisdiction of the City Courts and carry out other relevant functions in accordance with the appropriate law.

2) The organization of the Office shall be determined by law to be issued by the City Council.

29. Ethics and Anti-corruption Commission

The City Government shall have an Ethics and Anti-Corruption Commission to be established and function in accordance with law the City Council enacts.

## PART SIX
## SUB–CITY AND KEBELE

30. Sub-City

1) A sub-City shall, within the area allocated to it in accordance with the principle of decentralization, function as a municipalityin accordance with the central leadership of the City.

2) A sub-City shall administer Kebeles that are within its bounds.

3) Sub-Cities shall be responsible for having law and order observed within their locality.

4) The term of office of a sub-City Council shall be five years.

'31. Boundaries of sub-Cities and Kebeles

1) Without prejudice to the provisions of Article 5 of this Charter, the boundaries of sub-Cities and Kebeles shall be delimited by the City Council.

2) The City Council may either organize new sub-Cities or Kebeles, or reorganize existing ones taking into account the opinions of the respective residents, suitability of service delivery, urban development plan and the size of populations.

32. *Sub-City Council*

1) A sub-City Council, being accountable to residents of the respective sub-City and the City Council, shall:

(a) approve economic, social development and municipal service plans of the respective sub-City;

(b) elect, from among its members, the Spokesperson, the Deputy Spokesperson and the Secretary thereof;

(c) elect the Chief Executive and the Deputy Chief Executive of the sub-City from among its members recommended by the political party with the majority of seats in the council;

(d) approve the appointment of members of the Standing Committee of the respective sub-City upon nomination by the chief executive thereof;

(e) allocate the budget set aside to it by the City Council;

(f) constitute the committees of the council of Sub-City;

(g) receive, examine and decide upon the annual and periodic reports from the chief executive of the respective sub–City;

(h) issue internal regulations that govern the operations of the Sub-city council.

፪· የከተማው ምክር ቤት የክፍለ ከተማው ምክር ቤት ውሣኔ ሕገ-ወጥ ወይም የክፍለ ከተማውን ነዋሪ ጥቅም የሚጐዳ አደገኛ መሆኑን ሲያምን የክፍለ ከተማውን ምክር ቤት ይበትናል፣ የመልሶ ማቋቋም የጊዜ ገደብና የዕለት ተዕለት የአስፈፃሚነት ሥራ እየተከከናወነ ስለ ሚቆይበት ሁኔታ ይወስናል፣ ይህ በተመሳሳይ መልክ በቀበሌ ምክር ቤትም ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

፴፫· የክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈጉባዔ ፣ ምክትል አፈጉባዔ እና ፀሐፊ

.የክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈጉባዔ ፣ ምክትል አፈጉባዔ እና ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፲፰፣ ፲፱ እና ፳ የተደነገገው እንደየአግባቡ ተፈጻሚ ይሆናል።

፴፬· ስለክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ

፩· ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት እና ለከንቲባው ሆኖ የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ክፍለ ከተማውን ይመራል፣

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚው፣

ሀ) የቋሚ ኮሚቴ አባላትን ከምክር ቤት አባላት ወይም የምክር ቤት አባላት ካልሆኑት መካከል ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት አቅርቦ ሹመታቸውን ያፀድቃል፣

ለ) የክፍለ ከተማው ዓመታዊ እቅድና የበጀት ድልድል ሀሳብ በክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ ከተመከረበት በኋላ ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሐ) የክፍለ ከተማውን ቋሚ ኮሚቴ ይሰበስባል፣ ይመራል፣

መ) በክፍለ ከተማው ህግና ሥርዓት ያስከብራል ፣ ከክፍለ ከተማው አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ ችግር ሲያጋጥም ለከንቲባው ያሳውቃል፣

ሠ) ከክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅ የሚቀርብለትን ሪፖርት ይቀበላል፣ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣

ረ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አቅርቦት በክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ እንዲገመገም ያደርጋል፤ ውጤቱን ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት እና ለከን ቲባው ሪፖርት ያደርጋል፣

ሰ) በብሔራዊና የሕዝብ በዓላት ስነስርዓቶች ላይ ክፍለ ከተማውን ይወክላል፣

ሸ) ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ለከንቲባውና ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፣

ቀ) በክፍለ ከተማው ምክር ቤት እና በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዋንል።

፫· የዋና ሥራ አስፈጻሚው የሥራ ዘመን የክፍለ ከተማው የሥራ ዘመን ይሆናል። ሆኖም በራሱ ፈቃድ ወይም ጥፋት በመፈፀም ከምክር ቤቱ የሥራ ዘመኑ ከማለቁ በፊት በማንኛቸው ጊዜያት ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል። ይህም ሁኔታ ለምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚው ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

፴፭· የክፍለ ከተማ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ

ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ዋና አስፈፃሚ ሆኖ የክፍለ ከተማው ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ፤

፩· የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፤

፪· በዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፴፮· የክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ

፩· ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና በጋራ ለሚወሰነው ውሣኔም ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ሆኖ የክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ፣

2) The City Council shall dissolve a sub-City Council where it believes that the decisions thereof are unlawful or jeopardize the interest of residents of the respective sub-City. It shall also specify the deadline for re-institution of the sub-City Council and the conditions for meantime carrying out day-to-day executive functions. The same shall similarly be applicable as against a Kebele Council.

33. *Spokesperson, Deputy Spokesperson and Secretary of a sub-City Council*

The provisions of Articles 18, 19 and 20 of this Charter shall be applicable as concerns the powers and functions of the Spokesperson, the Deputy Spokesperson and the Secretary of a sub-City, respectively.

34. *Chief Executive of a sub-City*

1) The chief executive of a sub-City, being accountable to the respective sub-City Council and to the Mayor, shall head the respective sub-City.
2) Without prejudice to the generality of sub-Article (1) of this Article, the chief executive shall:
   (a) nominate Standing Committee members from within, and without of, members of the respective sub-City Council and have their appointment approved by the sub-City Council;
   (b) submit to the respective sub-City Council the proposal of the sub-City's annual plan and budgetary allocation after consultation thereon by the sub-City Standing Committee; implement same upon approval;
   (c) preside over the meetings of, and head, the respective Standing Committee;
   (d) ensure the observance of law and order in the respective sub-City and report to the Mayor in the event of a security problem beyond the sub-City's control;
   (e) receive, examine and decide on reports from the respective sub-City manager;
   (f) cause municipal service delivery to be evaluated by the respective sub-City Standing committee and report the outcome there of to the sub-City Council and the Mayor;
   (g) represent the respective sub-City at events of national and public holidays;
   (h) submit annual and periodic reports to the respective sub-City Council and the Mayor;
   (i) perform other functions assigned to him by respective sub-City Council and the Mayor.
3) The term of office of the chief executive shall be that of the sub-City Council provided that he may be removed from his post, prior to the end of such term, upon resignation or commission of fault. This situation shall also be applicable in respect of the deputy chief executive.

35. *Deputy Chief Executive of a sub-City*

The deputy chief executive of a sub-City, being accountable to the respective sub-City chief executive, shall:

1. act on behalf of the sub-City chief executive in case of absence or incapacitation of the latter;
2. perform other functions assigned to him by the chief executive.

36. *Standing Committee of a sub-City*

1) The Standing committee of a sub-City, being accountable to the sub-City chief executive and, for its joint decisions, to the sub-City Council, shall:

ሀ) በክፍለ ከተማው ዕቅድና የበጀት ድልደላ ሀሳብ ላይ ይመክራል፣
ለ) በክፍለ ከተማው ውስጥ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና የከተማው የበላይ አካላት ውሣኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
ሐ) በክፍለ ከተማው ምክር ቤትና በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፪· የቋሚ ኮሚቴው የሥራ ዘመን የክፍለ ከተማው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

፴፯· የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ

፩· ተጠሪነቱ ለከተማው ሥራ አስኪያጅ እና ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅ የክፍለ ከተማው የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈፃሚ በመሆን ይሠራል።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅ፣
ሀ) ከከተማው ሥራ አስኪያጅ ጋር በመመካከር በክፍለ ከተማው ደረጃ ያሉ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እና የአገልግሎት መስጫ አማራጮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
ለ) የክፍለ ከተማውን የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ሠራተኞች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፣
ሐ) በሥሩ ከሚሰሩ አካላት ኃላፊዎች የተውጣጣና በከተማው ሥራ አስኪያጅ በሚወሠነው መሠረት የሚሠራ የሥራ አመራር ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ይመራል፤
መ) ስለሥራው አፈፃፀም ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ለከተማው ሥራ አስኪያጅ እና ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፣
ሠ) ከከተማው ሥራ አስኪያጅ ጋር በመመካከር የክፍለ ከተማውን የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ዕቅድ በማዘጋጀት ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
ረ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከቱ ውሳኔ ዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤
ሰ) የቀበሌ ሥራ አስኪያጆችን በተወሠነ ጊዜ የሥራ ውል የሙያ ብቃትን መሠረት በማድረግ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤
ሸ) ከከተማው ሥራ አስኪያጅና ከክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፫· የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ በክፍለ ከተማው ምክር ቤት ስብሰባዎች ያለድምፅ መሳተፍ ይችላል።

፴፰· የቀበሌ ሥልጣንና ተግባር

፩· ቀበሌ የልማትና የህዝብ ቀጥተኛ ተሣትፎ ማዕከል በመሆንና በቀበሌ ደረጃ ሊሰጡ ለሚችሉ አገልግሎቶች ጣቢያ ሆኖ፣
ሀ) የቀበሌ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌው ነዋሪና ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ሆኖ በከተማው ምክር ቤት ተለይቶ የሚወሰን ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤
ለ) ነዋሪው በተቻለ መጠን አገልግሎት ባቅራቢያው የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

(a) deliberate on the plan and the budgetary allocation prposal for the respective sub-City;
(b) ensure the implementation, in the respective sub-City, of policies, proclamations, regulations and of decisions by the City's superior organs;
(c) perform other functions assigned to him by the Council and the chief executive of the respective sub-City.

2) The term of office of the Standing committee shall be that of the sub-City Council.

37. *Sub-City Manager*

1) The sub-City manager, being accountable to the City manager and to the sub-City chief executive, shall be the municipal services executive of the respective sub-City.
2) Without prejudice to the generality of sub-Article (1) of this Article, a sub-City manager shall:
(a) in consultation with the City manager, propose to the chief executive of the respective sub-City the utilization of municipal service organs and service delivery alternatives existing at the level of the sub-City; implement same upon approval;
(b) administer, in accordance with the applicable law, the employees of the municipal service organs of the respective sub-City;
(c) constitute and direct a management committee that consists of the heads of organs subordinated to him and functions as per determinations of the City manager;
(d) submit annual and periodic performance reports to the City manager and to the chief executive of the respective sub-City;
(e) prepare, in consultation with the City manager, the municipal services plan of the sub-City and submit it to the chief executive thereof; implement same upon approval;
(f) execute decisions concerning municipal services;
(g) hire, Kebele managers, in consideration of professional competence, as well as administer and discharge same under a contract of employment for a definite period;
(h) perform other functions assigned to him by the City manager and by the chief executive of the respective sub-City.

3) A sub-City manager may participate, without a vote, in meetings of the Council of the respective sub-City.

38. *Powers and Functions of a Kebele*

1) A Kebele, being a centre for development and direct popular participation as well as a location for the delivery of basic services, shall:
(a) with its council accountable to the resident there of and to the respective sub-City Council, have such powers and functions as to be specified by the city council,
(b) facilitate conditions in order for services to be available within reach of the respective residents.

፪· ቀበሌ ምክር ቤት ፣ አፈጉባዔ ፣ ፀሐፊ ፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ቋሚ ኮሚቴ ፣ ሥራ አስኪያጅ ፣ ማሕበራዊ ፍ/ቤት እና የተለያዩ አስፈጻሚ አካላት ይኖሩታል። ሥልጣንና ተግባራቸው በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ህግ ይወሰናል።

## ክፍል ሰባት

## የከተማው ፍርድ ቤቶችና የመዳኘት ሥልጣን የተሠጣቸው ሌሎች አካላት

፴፱· ፍርድ ቤቶች

የከተማው አስተዳደር የሚከተሉት ፍርድ ቤቶች ይኖሩታል፣

፩· የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች፤ እና

፪· የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች።

፵· የመዳኘት ሥልጣን ስለተሠጣቸው ሌሎች አካላት

የከተማው አስተዳደር የመዳኘት ሥልጣን የተሠጣቸው የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፤

፩· የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ፤

፪· የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት፤

፫· የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፤ እና

፬· የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ።

፵፩· የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፤

፩· የፍትሐ ብሔር ዳኝነት ሥልጣን

ሀ) የከተማውን መሪ ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የይዞታ ባለመብትነት፣ የፈቃድ አሰጣጥ ወይም የቦታ አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች፣

ለ) ከከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት የመቆጣጠር ሥልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮች፣

ሐ) በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፶፪ በተመለከቱ የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ክሶች፣

መ) የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸውን አስተዳደራዊ ውሎች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች፤

ሠ) በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ወይም በሥሩ ባሉ ተቋማት መካከል የሚነሱ ክርክሮች፤

ረ) የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግሥት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮች፤

ሰ) የስም ለውጥ አቤቱታ፤

ሸ) የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ፤

ቀ) የመጥፋትና የሞት ውሳኔ አቤቱታ።

፪· የወንጀል/የደንብ መተላለፍ ዳኝነት ሥልጣን

ሀ) በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፶፪ በተመለከቱ የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ የወንጀል ጉዳዮች፤

ለ) የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች፤

ሐ) በፌዴራል ወንጀሎች ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የጊዜ ቀጠሮ እና የዋስትና ጉዳዮች፤

መ) ሌሎች የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት የሚጣሉ የደንብ መተላለፍ ቅጣቶችን የማስፈፀም ጉዳዮች።

፵፪· የዳኝነት ሥልጣን ግጭትና ሰበር

፩· በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣንና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን መካከል የሥልጣን ግጭት ሲያጋጥም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኛል።

2) A Kebele shall have a Council, a Spokesperson, a Secretary, a Chief Executive, a Standing Committee, a Manager, a Social Court and different executive bodies. Their respective powers and functions are to be determined by law which the City Council shall issue.

## PART SEVEN

## City Courts and other Bodies with Judiciial Power

39. *Courts*

The City Government shall have the following Courts:

1) the Addis Aababa City Courts; and
2) Kebele Social Courts.

40. *Other Bodies with Judicial Power*

The City Government shall have the following bodies vested with judicial power:

1) Labour Relations Board;
2) Civil Service Tribunal;
3) Tax Appeal Commission; and
4) Urban Land Clearance Matters Appeal Commission.

41. *Jurisdiction of the Addis Ababa City Courts*

The Addis Ababa City Courts shall have jurisdiction over the following matters:

1. Civil Jurisdiction
   (a) suits on possessory right, issuance of permit or land use as relating to the enforcement of the city Master Plan;
   (b) suits brought in connection with the regulatory powers and functions of executive bodies of the City Government;
   (c) suits on fiscal matters set out under Article 52 of this Charter;
   (d) suits brought in connection with administrative contracts concluded by executive bodies of the City government or by enterprises under the ownership thereof;
   (e) disputes arising between executive bodies of the City Government or between other organs thereof;
   (f) suits brought in connection with government - owned houses administered by the City Government;
   (g) applications for change of name;
   (h) applications for succession certificate; and
   (i) applications for the declaration of absence and death.
2) Criminal and Petty Offence Jurisdiction
   (a) Charges brought in connection with fiscal matters set out under Article 52 of this Charter;
   (b) cases of petty offence;
   (c) without prejudice to the jurisdiction of Federal Courts on the substance of Federal offences, remand in custody and bail applications;
   (d) without prejudice to the other provisions of this Article, cases of execution of penalties, for petty offences, imposed by executive bodies of the City Government.

42. *Conflict of Jurisdiction and Power of Cassation*

1) The Federal Supreme Court shall decide on conflict of jurisdiction that may arise between the Addis Ababa City Courts and Federal Courts.

፪· የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጣቸው ጉዳዮች መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ወደዚሁ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ጉዳዮችን ሊያቀርብ ይችላል።

፫· በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለው የሚል ወገን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

፵፫· <u>የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና አሠራር</u>

፩· የከተማው ፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ይኖራቸዋል።

፪· የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በከተማው ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።

፫· የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የመዳኘት ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች አካላት የተወሰኑ ጉዳዮችን በይግባኝ ያያል።

፬· የከተማ ፍርድ ቤቶች ሥራቸውን የሚያካሂዱት አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ይሆናል።

፭· በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፮· የከተማ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት የከተማው ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ ይወሰናል።

፵፬· <u>የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ</u>

፩· የከተማ ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥራ አካሄድ የሚመራ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በከተማው ምክር ቤት ይቋቋማል፣ ዝርዝሩ በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

፪· በጉባዔው ውስጥ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተወካይ ይኖራል።

፵፭· <u>የዳኞች ሹመትና የሥራ ዘመን</u>

፩· የከተማው የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የሚሾሙ ዕጩ ዳኞች ዝርዝር ለከተማው ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በዕጩዎች ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅና ይህንኑ አስተያየት ከራሱ አስተያየት ጋር በማያያዝ በከንቲባው አማካይነት ለከተማው ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አስተያየቱን በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የዕጩዎቹ ዝርዝር ለሹመት ለከተማው ምክር ቤት ይቀርባል።

፪· ዳኞች ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ከፈቃዳቸው ውጭ ከዳኝነት ሥራ አይነሱም፣

(ሀ) የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ዳኛው የዲስፒሊን ደንቦችን በመጣሱ ወይም የሙያ ብቃትና ጥራት በማጓደሉ ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበት ሲወስን፣ ወይም

(ለ) በሕመም ምክንያት ዳኛው ሥራውን መቀጠል እንደማይችል ሲወሰን፣ እና

(ሐ) የከተማው ምክር ቤት ከግማሽ በላይ በሆነ ድምፅ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔውን ውሣኔ ሲያጸድቀው።

፵፮· <u>የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ</u>

የከተማው አስተዳደር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ሥልጣን፣ አደረጃጀትና አሠራር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፹፭ (እንደተሻሻለ) በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

፵፯· <u>የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት</u>

፩· የከተማው አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የሚቀርቡለትን የአስተዳደሩን ሠራተኞች ጉዳይ በይግባኝ የማየት ሥልጣን አለው።

2) A party alleging a fundamental error of law in a final judgement of the Addis Ababa City Appellate Court may apply before the Cassation Division thereof.

3) A party alleging a fundamental error of law in a final judgemnt rendered by the Addis Ababa City courts may apply for cassation before the Federal Supreme Court.

43. *Organization and Procedure of the Addis Ababa City courts.*

1) The City courts shall have a First-Instance Court and an Appellate Court.

2) The First-Instance Court shall have first-instance jurisdiction over matters falling under the jurisdiction of the City Courts.

3) The Appellate Court shall hear appeals from the decisions of the First-Instance Court and other bodies vested with judicial power.

4) The City courts shall adjudicate in accordance with applicable laws.

5) Without prejudice to the provisions on application for cassation under Article 42 hereinabove, decisions rendered by the Appellate Court shall be final.

6) The organization of the City Courts is to be determined by law which the City Council shall issue.

44. *judicial Administration Commission of the Addis Ababa City Courts.*

1) A Judicial Administration commission that directs operation of judicial matters by the City Courts shall be constituted; details thereof are to be specified by law which the City Council shall issue.

2) There shall be a representative of Federal Courts on the Commission.

45. *Appointment and Term of Office of Judges*

1) The City Judicial Administration Commission shall, before submitting a shortlist to the City Council to have it appoint judges of the City Courts, solicit the Federal Judicial Administration Commission's opinion on the candidates and, through the Mayor, forward said opinion, together with its recommendations, to the City Council, Where the Federal Judical Administration Commission does not forward its opinion within three months, the shortlist for appointment shall be submitted to the City Council.

2) No judge shall be removed from his office, without consenting thereto, except under the following conditions'

   a) where the Judicial Administration Commission decides to remove him for violation of disciplinary rules or on grounds of professional incompetence or poor performance; or

   b) where it is decided that he can no longer carry out his duties on account of illness; and

   c) where the City Council approves, by majority vote, the decision of the Judical Administration commission.

46. *Labour Relations Board*

The provisions of the Labour Proclamation No. 42/1993 (as amended) shall be applicable with respect to jurisdication, organization and procedure of the Labour Relations Board of the City Government.

47. *Civil Service Tribunal*

1) The Civl Service Tribunal of the City Government has the power to hear appeals loged, pursuant to Civil Servie Laws, by Civil Servants under the City Government.

፪· የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አደረጃጀትና አሠራር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

፵፰· የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ

፩ የከተማው የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በከተማው አስተ ዳደር የሚሰበሰቡ ግብሮችና ቀረጦችን በተመለከተ የሚ ቀርበለትን ይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል።

፪· የጉባዔው አደረጃጀትና አሠራር በግብር ሕጎች የተደነ ገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

፵፱· የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ

፩· የአዲስ አበባ ከተማ የቦታ ማስለቀቅ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የከተማ ቦታ ስለመያዝ እንደገና ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፪/፲፱፻፺፬ መሠረት ይሠራል።

፪· የጉባዔው አደረጃጀትና አሠራር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

፶· የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች

፩· የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች ግምታቸው ከብር ፭ሺ/ አምስት ሺህ/ ያልበለጡ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮችን የማየት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

፪· የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች የከተማውን የሃይጂንና የጤና አጠባበቅ ደንብ እና ሌሎችም ተመሳሳይ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ለማየት የሚኖራቸው ሥልጣን በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው እንደተ ጠበቀ ሆኖ የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡ አቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን ለከተማው የመጀ መሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል። በዚህ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሰኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፬· የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡአቸው ውሳኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ካለባቸው ለከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊቀርብባቸው ይችላል። የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፭· የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና አሠራር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

## ክፍል ስምንት
## ስለ በጀት እና ፋይናንስ

፶፩· የበጀት ዓመት

የከተማው አስተዳደር የበጀት ዓመት የፌዴራሉ መንግሥት የበጀት ዓመት ይሆናል።

፶፪· የፋይናንስ ሥልጣን

የከተማው አስተዳደር የሚከተለው የፋይናንስ ሥልጣን ይኖረዋል፤

፩· የኦሮሚያ ክልልን፣ የፌዴራል መንግሥትንና የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቀጣሪዎችን ሳይጨምር በከተማው ክልል ውስጥ በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የሥራ ግብር በሕግ መሠረት ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

፪· በከተማው ውስጥ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፤ ይሰበስባል፤

፫· በከተማው ውስጥ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል፤ይሰበ ስባል፤

፬· በከተማው በሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የኤክሳይዝና የተርንኦቨር ታክስ በሕግ መሠረት ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

፭· በከተማው ከሚኖሩ ግለሰብ ነጋዴዎች እና በከተማው ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ በፌዴራል መንግሥት ተሰብስቦ ለከተማው አስተዳደር ይሰጣል።

፮· በከተማው ውስጥ የከተማ ቦታ ኪራይና የቤት ግብር ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፯· በከተማው ውስጥ ከተከራዩ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ የገቢ ግብር በሕግ መሠረት ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

፰· በከተማ ከሚፈጸሙ ውሎችና ስምምነቶች እንዲሁም ከንብረት ባለቤትነት ስም ምዝገባ ላይ የቴምብር ቀረጥ በሕግ መሠረት ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

2) The organization and procedure of the civil service tribunal is to be determined by law the City Council shall issue.

48. *Tax Appeal commission*

1) The Tax Appeal commission of the City shall have the power to hear appeals lodged with it concerning taxes and duties the City government collects.
2) Without prejudice to the provisions of tax laws, the organization and mode of operation of the commission is to be determined by law the City Council shall issue.

49. *Urban Land Clearance Matters Appeal Commission*

1) The Addis Ababa City Urban Land Clearance Matters Appeal Commission shall operate in accordance with the Re-enactment of Urban Lands Lease Holding Proclamation No. 272/2002.
2) The organization and mode of operation of the Commission is to be determined by law the City Council shall issue.

50. *Kebele Social Courts*

1) Kebele Social Courts shall have jurisdication over cases of property and money claimed where the amount involved does not exeed Birr 5000(five thousand Birr).
2) The jurisdication of Kebele Social Courts over contraventions of the City's hygiene and public health Regulations and similar other petty offences is to be determined by law the City Council shall issue.
3) Without prejudice to the provisions of sub-Article (4) of this Article, a party dissatisfied with the decision of a Kebele Social Court may appeal to the corresponding First-Instance Court of the City. The decision of the latter Court shall be final.
4) Where a final judgement rendered by the City's First-Instance Court in a case lodged with it on appeal contains a fundamental error of law, application for cassation thereon may be brought before the City's Appellate Court.
5) The organization and procedure of Kebele Social Courts is to be determined by law the City Council shall issue.

## PART EIGHT
## BUDGET AND FINANCE

51. *Fiscal Year*

The fiscal year of the City Government shall be that of the Federal Government.

52. *Fiscal Power*

The City Government shall, in accordance with relevant laws, exercise the following fiscal powers:

1) assess and collect tax on income from employment within the City, excluding employees of Oromia Region, of the Federal Government and of Federal pulbic enterprises;
2) fix and collect land use fee within the City;
3) levey tax on income from agricultural activities within the City;
4) assess and collect profit, excise and turnover taxes from indivdual businessmen trading in theCity;
5) receive value added tax collected by the Federal Government from individual businessmen trading in, and public enterprises owned by, the City;
6) fix and collect urban land rent and levey urban house tax in the City;
7) assess and collect tax on income from rented houses and other properties in the City;
8) assess and collect stamp duty on contracts and agreements as well as on title deeds registration executed in the City;

፱· በከተማ አስተዳደር ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የኤክሳይዝና የተርን ኦቨር ታክስ በሕግ መሠረት ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፲· የከተማውን መንገዶች ከሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች የመንገድ መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

፲፩· በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የመን ግሥት ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

፲፪· በከተማው ውስጥ በሚካሄዱ አነስተኛ የማዕድን ሥራዎች ላይ የማዕድን ገቢ ግብር፣ የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ ክፍያዎችን በሕግ መሠረት ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

፲፫· በከተማ ውስጥ የደን መጠቀሚያ ሮያሊቲ ክፍያ በሕግ መሠረት ይወስናል ፣ ይሰበስባል፤

፲፬· በከተማ አስተዳደር ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

፲፭· የከተማ ነክ ታክሶች፣ ቀረጦችንና የአገልግሎት ክፍያ ዎችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

፲፮· በከተማ ውስጥ የፈጠራ መብትን በማከራየት በሚገኝ ጥቅም ላይ የገቢ ግብር በሕግ መሠረት ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

፲፯· በከተማው ውስጥ በሚገኝ ንብረት የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር በሕግ መሠረት ይወስናል፣ ይሰበስባል።

፶፫· ገቢ ማስገኛ

የከተማው አስተዳደር፣

፩· በሕግ እስካልተከለከለ ድረስ ከተማው ከሚያንቀሳቅሰው ወይም ከልዩ ፈቃድ የገቢ ማግኛ ተግባራት በማከናወን፣ ከጋራ ኢንቬስትመንት፣ ከፈንድ ኢንቬስትመንት፣ ከኪራይና፣ ከለጋሾች ገንዘብ በማሰባሰብ ለከተማው ገቢ ያስገኛል፤

፪· ክፍያ በሚያስገኙ ልዩ ልዩ ተግባራት ውል በመዋዋል መሳተፍ ይችላል።

፶፬· ብድር

፩· የከተማው አስተዳደር የፌዴራል መንግሥት በሚፈ ቅደው መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች በአጭርና በረጅም ጊዜ ክፍያ ቀጥታ ብድር ወይም የዋስትና ሰነዶችን በመሸጥ ሊበደር ይችላል።

፪· ብድሩ የሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ መረጋጋትንና የከተማው አስተዳደር በየወቅቱና በቋሚነት ተግባርና ግዴታዎቹን ለማሟላት የሚያስፈልገውን የገንዘብ አቅም የማይጎዳ መሆኑን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል።

፫· የከተማው አስተዳደር ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ምንጭ ብድር የሚገኝበትን ሁኔታ በማጥናት የፌዴራሉ መንግሥት እንዲበደርለት ይጠይቃል።

፬· ክፍለ ከተሞችና ቀበሌዎች መበደር አይችሉም።

፭· በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ፣ በከተማው አስተዳደር፣ በክፍለ ከተማዎችና ቀበሌዎች ተሳታፊነት የከተማው አስተዳደር የቁጠባና ልማት ባንክ በሕግ መሠረት ሊያቋቁም ይችላል። የባንኩ አሠራር እንደሌሎች መደበኛ ባንኮች ይሆናል።

፶፭· የከተማው አስተዳደር ከፌዴራል መንግሥት ስለሚያገኘው የፋይናንስ ድጋፍ

፩· የከተማው አስተዳደር ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት ይችል ዘንድ እንደአስፈላጊነቱ የአስቸኳይ ጊዜ የማቋቋሚያና የልማት እርዳታ በፌዴራል መንግሥቱ ሊሰጠው ይችላል። እንዲሁም ልማታዊ ጠቀሜታቸው ሀገር አቀፍ እንደምታ ላላቸው ፕሮግራሞች የሚያስፈልገውን ወጪ የፌዴራል መንግሥቱ ሊያግዘው ይችላል።

፪· በፌዴራል መንግሥት የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍና ብድር በተመለከተ የፌዴራል መንግሥቱ ቁጥጥር አዲት ለማድረግና ገንዘቡ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለመቆ ጣጠር ሥልጣን ይኖረዋል።

9) assess and collect profit, excise and turnover taxes from public enterprises owned by itself;
10) fix and collect road-user-vehicles charge in the City;
11) fix and collect rentals from houses and other properties owned by itself;
12) assess and collect income tax, royalty and land rentals on small-scale mining operations undertaken within the City;
13) fix and collect royalty on use of forest resources within the City;
14) fix and collect fees on licenses issued, and services delivered, by itsjelf;
15) levy municipal taxes and duties as well as fix and collect service charges thereof;
16) assess and collect income tax on gains from renting of patent rights within the City;
17) assess and collect capaital gains tax on property situate in the City.

53. *Revenue Generation*

The City Government:

1) shall obtain its revenue from juridical bodies under its charge, income generating activities where it hold the special permit required thereto, joint investment, fund investment, rentals and from donations; provided there is no legal prohibition in respect thereof.
2) may, through contractual agreement, undertake diverse activities for gain.

54. *Loans*

1) The City Government may, as per authorization by the Federal Government, borrow from domestic sources directly or by way of selling bonds, on short and long repayment terms.
2) In case of any loan, account should be taken of the non-endangerment of the country's macro-economic stability as well as of the City Government's financial capability to discharge its functions and obligations both intermittently and perpetually.
3) The City Government shall identify international credit sources and solicit the Federal Government to take loans therfrom on its behalf.
4) Sub-Cities and Kebeles may not take loans.
5) The City Government may, in accordance with the law, establish a Savings and Development Bank in partnership with governmental and nongovernmental organizations as well as with sub-Cities and Kebeles. The operations of the Bank shall be as that of any other common bank.

55. *Finacial support from the Federal Government*

1) The City Government may, as found necessary for it to properly discharge its responsibilities, be granted with emergency, rehabilitation and development aid by the Federal Government.It may also receive financial assistance from the Federal Government for expenditures on programmes having a developmental value of countrywide effect.
2) The Federal Government shall have auditing and supervision powers in respect of the proper utilization of the financial support and loans it extends to the City Government.

፶፮. በጎ አድራጎት

የከተማው አስተዳደር ባለአደራና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ማቋቋም እና ሌሎች በሕግ መሠረት እንዲያቋቁሙ መፍቀድ ይችላል።

፶፯. ያልተማከለ የፋይናንስ ሥርዓት

፩. የክፍለ ከተማዎች የገቢ ክፍፍል ሥርዓት ተወዳዳሪነትንና ውጤታማነትን የሚያበረታታ እንዲሁም ፍትሃዊነትን መሠረት ባደረገ ቀመር እንዲከናወን ይደረጋል።

፪. ክፍለ ከተማዎች ከከተማው ለተወሰነ ልዩ ሥራ የተመደበና የበጀት ድጎማ ይሰጣቸዋል። ከድጎማ በጀቱ የተወሰነው በሥራቸው ለተዋቀሩት አስፈፃሚ አካላትና ለቀበሌዎች ይከፋፈላል። ክፍፍሉም የአገልግሎት አቅርቦትና በልማት ወደኋላ የቀሩ ቀበሌዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

፫. የከተማው ምክር ቤት በልዩ ሁኔታ እንዲበረታቱ ለሚፈልጋቸው ፕሮጀክቶች ውጪ መሸፈኛ ለክፍለ ከተማዎችና ቀበሌዎች ከቀመር ውጪ ድጎማ ሊሰጥ ይችላል።

፬. የከተማው የልማት ድርጅቶች መነሻ ካፒታል ይመድብላቸዋል።

፭. ከከተማው ገቢዎች መካከል በክፍለ ከተማ ተሰብስበው በጥቅም ላይ የሚውሉት በከተማው ምክር ቤት ይወሰናሉ።

፶፰. የፋይናንስ አስተዳደር

፩. የከተማው የፋይናንስ አስተዳደር ተቀባይነት ባላቸው የሂሣብ አያያዝ ሥርአቶች፣ የሀገሪቱ የፋይናንስ ህግና የከተማው ምክር ቤት ይህንኑ አስመልክቶ በሚያወጣው ሕግ መሠረት ይከናወናል።

፪. የከተማው አስተዳደር የከተማ ሀብት መጠበቁንና በህግ መሠረት በሥራ ላይ መዋሉን የሚያረጋግጥ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ይኖረዋል።

፫. ከንቲባው ወቅታዊና አመታዊ የፋይናንስ ሪፖርት ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል። የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች በተመሳሳይ መልኩ ለክፍለ ከተማ ምክር ቤቶች ሪፖርት ያቀርባሉ።

፬. የከተማው አስተዳደር እና ክፍለ ከተማዎች የተሟላ ኦርጅናል ገንዘብ ነክ ሰነዶች እንዲሁም ትክክለኛና የተሟላ የሂሣብ መዝገብ ይይዛሉ።

፭. ማንኛውም የተሰበሰበ ገንዘብ በፋይናንስ ህግ በተፈቀደው መሠረት በባንክ ሂሣብ ውስጥ ይቀመጣል።

፮. የከተማው አስተዳደርና ክፍለ ከተማዎች በስማቸው የሚከፈት የባንክ ሂሣብ ይኖራቸዋል።

፯. የከተማው አስተዳደር በህግ መሠረት የግብር፣ የወለድና የመቀጫ ምሕረት የማድረግ እንዲሁም ዕዳን የመሠረዝ ሥልጣን ይኖረዋል።

፶፱. የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር

፩. የከተማው የበጀት አስተዳደር የፌዴራል መንግሥቱን የበጀት መርህ የተከተለ ይሆናል።

፪. የከተማው በጀት በግልጽና ነዋሪውን በሚያሳትፍ መልኩ ይዘጋጃል። የበጀት ጥያቄው ከመጽደቁ በፊት ባለበጀት መሥሪያ ቤቶችንና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አስተያየታቸውን ይሰጡበታል፣ የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ነዋሪው እንዲሳተፍ ይደረጋል። በበጀት ላይ የሚደረጉ የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ለነዋሪው ክፍት ይሆናሉ። በአዳዲስ የስራ ፕሮግራሞች፣ የካፒታል ወጪዎችና ገቢዎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶች ነዋሪው እንዲያውቃቸው ይደረጋሉ።

፫. የከተማው ምክር ቤት መጠባበቂያ በጀት ይመድባል። ከንቲባው የከተማውን ካቢኔ በማሳወቅ መጠባበቂያውን ለተፈላጊው ሥራ መድቦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያውላል፣ ለከተማ ምክር ቤትም ያሳውቃል።

56. *Foundations*

The City Government may establish trusts and foundations and authorize others to establish same in accordance with the law.

57. *Decentralized Financial System*

1) The revenue-sharing system for sub-Cities shall be effected according to a formula which enhances competitiveness and effectivness as well as rests on equity.
2) Sub-Cities shall receive, from the City Council, budgetary subsidy allocated for a particular task of special nature. A certain amount of such budgetary subsidy shall be apportioned to executive organs and Kebeles respectively consitituted under the Sub-Cities. The apportionment shall take account of service delivery and Kebeles that are under-developed.
3) The City Counil may grant special subsidy to sub-Cities and Kebele to cover the expenditure of projects that it desires to promote execeptionally.
4) Public enterprise of the City Government shall be allocated with initial capital.
5) Such revenues of the City Government as are to be collected and directly utilized by sub-Cities shall be specified by the City Council.

58. *Financial Administration*

1) The financial administration of the City shall be in accordance with accepted accounting norms, the country's finance laws and with the respective law to be issued by the City Council.
2) The City Government shall have an internal control system to ensure the safegurading and lawful utilization of the City's resources.
3) The Mayor shall submit periodic and annual reports to the City Council. Sub-city chief executives shall similarly submit reports to the respectives sub-City Council.
4) The City Government and sub-Cities shall maintain complete and orginal financial documents as well as accurate and complete books of account.
5) All funds collected shall, as per stipulations under finance laws, be deposited in bank accounts.
6) The City Government and sub-Cities shall have bank accounts opened in their respective names.
7) The City Government shall have power to waive payment of taxes, interests and fines as well as to write off debts, in accordance with the law.

59. *Budget Preparation and Administration*

1) The City's budgetary administration shall follow the budgetary principles of the Federal Government.
2) The City's budget shall be prepared transparently and through the participation of residents. Budgeted offices and other concerned organs shall comment on abudgetary proposal before it is approved. Mass media shall be used for the participation of residents Budgetary meetings of the Council shallbe open to residents. Its deliberations on new work programmes, capital expenditures and incomes shall be notified to residents.
3) The City Council shall allocate a contingency budget. The Mayor shall, subject to notifying the City Cabinet, approtion such budget for necessary works properly expend it thereon and subsequently report the matter to the City Council.

፷· የከተማው የልማት ድርጅቶች

፩· የከተማው የልማት ድርጅቶች በቦርድ ይመራሉ።

፪· የከተማው የልማት ድርጅቶች አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚተዳደሩ ተቋማት ናቸው።

፫· ከንቲባው የቦርድ ሰብሳቢዎችንና አባላትን የከተማው ሥራ አስኪያጅ ከሚያቀርባቸው እጩዎች መካከል ይሰይማል። የቦርዱ ተጠሪነትም ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ይሆናል።

፬· የልማት ድርጅቶች ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ሪፖርት ያቀርባሉ።

## ክፍል ዘጠኝ
## መስተዳድራዊ ግንኙነት

፷፩· የከተማው አስተዳደርና የፌዴራል መንግሥት ግንኙነት

፩· የከተማው አስተዳደር ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር የሚኖረው ግንኙነት የፌዴራሉን መንግሥት ኃላፊነት ያገናዘበ መሆን አለበት።

፪· የከተማው አስተዳደር የፌዴራል መንግሥት አካል ነው። ፀጥታን ፣ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን ፣ የፌዴራል መንግሥት ፖሊሲዎችን ፣ ሕጐችንና የሥራ ደረጃዎችን በተመለከተ ለፌዴራሉ መንግሥት ተጠሪ ነው።

፫· የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወስነው መሠረት ሕገመንግሥቱን አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር በከተማው ምክር ቤት ሲፈፀም ወይም የከተማው አስተዳደር ፀጥታንና ድንገተኛ ሁኔታን መቆጣጠር ሲያቅተው የፌዴራል መንግሥት የከተማውን አስተዳደር የማፍረስና የሽግግር አስተዳደር የማቋቋም ሥልጣን አለው።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ሲወሠን የፌዴራል መንግሥት በሥልጣን ላይ ያለውን አስተዳደር ያሰናብታል፣ ለከተማው የሽግግር አስተዳደር ያደራጃል፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተቀመጠው የጊዜ ገደብና ውሣኔ መሠረት ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል።

፭· የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የፌዴራል መንግሥትን በመወከል የከተማውን አስተዳደር ሥራ ይከታተላል፣ የከተማውን አቅም ግንባታ ሥራ ይደግፋል።

፮· የከተማው አስተዳደር ዕቅዱን ፣ በጀቱንና የከተማውን አጠቃላይ ሁኔታ በተመለከተ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አመታዊና ወቅታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል።

፯· በከተማው ውስጥ የሚገኙት የፌዴራል መንግሥት አካላት የከተማውን አዋጆችና ደንቦች የማክበር ግዴታ አለባቸው።

፰· ከተማውን የሚመለከቱ በፌዴራል ተቋማት የሚካሄዱ አገልግሎቶች ከከተማው አስተዳደር ጋር በቅንጅትና በስምምነት ይፈፀማሉ።

፷፪· የከተማው አስተዳደርና የኦሮሚያ ክልል ግንኙነት

፩· የከተማው አስተዳደር ከኦሮሚያ ክልል ጋር ፍሬያማ ትብብርን መሠረት ያደረገ ግንኙነት ይኖረዋል።

፪· በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥት አንቀፅ ፵፱(፭) መሠረት የኦሮሚያ ክልል ልዩ ጥቅም የተጠበቀ ነው። ዝርዝሩ በከተማው አስተዳደርና በኦሮሚያ ክልል መካከል በሚደረግ ስምምነት ወይም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

፷፫· ከሌሎች ከተሞችና ክልሎች ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

፩· የከተማው አስተዳደር ከሀገሪቱ ክልሎችና ከተሞች እንዲሁም ከውጭ ሀገር ከተሞች ጋር ግንኙነት መፍጠር ይችላል፤

፪· በአገር ውስጥ የከተማው አስተዳደር ከሌሎች ከተሞችና ክልሎች ጋር የነዋሪዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ በፖሊሲዎች፣ በመሠረተ ልማትና በአገልግሎት አቅርቦት የልምድ ልውውጥ እና ትብብር ለማድረግ ይችላል፤

60. *Public Enterprises of the City*

1) Public enterprises of the City shall be directed by a board.
2) Public enterprises of the City shall be subject to applicable laws.
3) The Mayor shall designate the chairpersons and members from among candidates nom inated by the City; the boards shall be accountable to the City Manager.
4) Public enterprises shall report to the City Manager.

## PART NINE
## INTERGOVERNMENTAL RELATIONSHIP

61. *The City Government and the Federal Government*

1) The relationship that the City Government maintains with the Federal Government shall take cognizance of the responsibilities of the latter.
2) The City Government is a component part of the Federal Government. It shall be accountable to the Federal Government concerning security, diplomatic relations as well as policies, laws and standards thereof.
3) The Federal Government has the power to dissolve the City Government and to constitute a transitional government, as per the decision of the House of Peoples' Representatives, where an act endangering the Constitution is committed by the City Council or where the City Government fails to manage security matters and emergency situations.
4) The Federal Government shall remove the City Government in power and organize a transitional government thereof, where decided as under sub-Article (3) of this Article. The Prime Minister shall ensure that such execution conforms to the decision given by the House of Peoples' Representatives and to the time-limit thereby set.
5) The Ministry of Federal Affairs shall, by way of representing the Federal Government, follow up the activities of the City Government and support the capacity-building undertakings of the City.
6) The City Government shall submit to the Ministry of Federal Affairs annual and periodic performance reports on its plan, budget and the overall state of affairs of the City.
7) Federal Government organs situated in the City shall have the duty to observe proclamations and Regulations issued by the City Government.
8) Services provided to the City by Federal organs shall be run in collaboration and agreement with the City Government.

62. The Relashionship of the City Government and the Oromia Region

1) The City Govenment shall have such a relationship with the Oromia Region as rests on fruitful cooperation.
2) The special interest of the Oromia Region shall be respected as provided under Article 49(5) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia. The details thereof shall be set out by agreement to be made between the City Government and the Oromia Region or by law to be issued by the House of Peoples' representatives.

63. Relations with Other Cities and Regions

1) The City Government may establish relations with other local cities and the regions as well as with foreign cities.
2) The City Government may undertake, locally, excahnge of experience and cooperation with other citeis and the regions in respect of policies, infrastructure and service delivery in order to promote the interest of residents.

፫· ከሀገር ውጭ ከሚገኙ እህት ከተሞች ጋር ግንኙነት ለመመስረት ይችላል፣ በተለይም የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ፣ የባህል ልውውጥ፣ የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ፣ የዕቃዎች ልውውጥ ፣ ሥልጠና ፣ የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ማስተዋወቅ የሚያካትት ሊሆን ይችላል።

## ክፍል አሥር
## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

፷፬· የሙከራ ሥራ
የከተማው አስተዳደር ከሥልጣንና ተግባሩ ጋር በተያያዘ የሙከራ ሥራዎችን እንዲያካሂድ በከተማው ምክር ቤት ሊፈቀድለት ይችላል። የሙከራ ስራው ክንዋኔና ግምገማ ምክር ቤቱ በሚወስነው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ይካሄዳል።

፷፭· ቻርተሩን ስለማሻሻል
የቻርተሩ ማሻሻያ ሃሣብ በከተማው በምክር ቤት ወይም አግባብ ባለው የፌዴራል መንግስት አካል ሊቀርብ ይችላል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቻርተሩን የማሻሻያ ሃሣብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሣኔ እንዲያገኝ ያደርጋል።

፷፮· የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች
፩· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር እንደተቋቋመ ይህ ቻርተር ከመፅናቱ በፊት በየደረጃው ተቋቁመው የነበሩት ምክር ቤቶችና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች ይበተናሉ።
፪· እስከ ተከታዩ የምክር ቤት ምርጫ የሚቆይ ጊዜያዊ የከተማ አስተዳደር በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማል፣ ሥራውንም ይረከባል። ጊዜያዊ አስተዳደሩ በዚህ ቻርተር ለከተማው ምክር ቤት እና ለከተማው ካቢኔ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል። የጊዜያዊ አስተዳደሩ ከንቲባም በዚህ ቻርተር ለከንቲባው የተሰጠ ሙሉ ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።
፫· ጊዜያዊ አስተዳደሩ፣
ሀ) የክፍለ ከተማና የቀበሌ ጊዜያዊ አስተዳደሮችን ይሰይማል፤
ለ) የክፍለ ከተማና የቀበሌ አከላለልን በዚህ ቻርተር መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል፤
ሐ) የከተማውን አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች እንደገና ያደራጃል፣ ሠራተኞችን በሚያጸድቀው መዋቅር መሠረት እንደገና ይመድባል፣ ይቀጥራል ፣ ያሰናብታል፤
መ) ለሽግግሩ ወቅት በልማት ፣ በዲሞክራሲ ግንባታና በአገልግሎት አቅርቦት የነዋሪው የተደራጀ ተሣትፎ ለማጐልበትና የህዝቡን ጥቅም የሚያስጠብቁ ውሣኔዎች ለመወሠን እንዲቻል ከነዋሪዎችና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተወከሉ ሠዎች የሚሣተፉበት አማካሪ ምክር ቤቶች በከተማው ፣ በክፍለከተማ እና በቀበሌ ደረጃ ሊያቋቁም ይችላል፣ ዝርዝሩም በጊዜያዊ አስተዳደር ይወሰናል፤
፬· ጊዜያዊ አስተዳደሩ በሥራ ላይ ያሉትን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ይመድባል፣ ያሰለጥናል፣ እንዳስፈላጊነቱ ለማሰናበት ይችላል። ጊዜያዊ አስተዳደሩ የአመራረ አባላቱን በሹመትና በዝውውር ይመድባል፣ ሲያስፈልግም ያሰናብታል።
፭· የጊዜያዊ አስተዳደሩ በሚያጸድቀው መዋቅር መሠረት የከተማው አስተዳደር አካላት ወይም ተቋማት በሕግ መሠረት በሌላ አካላት ሲተኩ ወይም ሲዋሃዱ መብትና ግዴታቸው ለሚቋቋሙት አካላት ወይም ተቋማት ይተላለፋሉ ወይም እንደአግባቡ በጊዜያዊ አስተዳደሩ ይወሰናል።

3) The City Government may establish such relations with foreign sister cities as would, particulary, involve economic and technical cooperation cultural exchange, voluntary service excahnge of goods, training as well as promotion of tourism and investment opportunities.

## PART TEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

64. *Experimentation*
The City Government may be authorized by the City Council to undertake experiementation in connection with its powers and functions. The undertaking and evaluation of such experimentation shall be effected as per the time table the Council sets thereto.

65. *Amendment of the Charter*
Amendment proposals on this Charter may be initiated by the City Council or by the appropriate organ of the Federal Government. The Prime Minister shall, subject to bringing such proposals before the Council of Ministers and approval thereof, forward the matter to the House of Peoples' Representatives for its decision thereon.

66. *Transitory Provisions*
1) Councils and Executive Committees of different levels, constitued under the City Governemtn before the coming into force of this Charter, shall be dissolved upon establishement of the Provisional Government of the City in accordance with sub-Article (2) of this Article.
2) A Provisional City Government to stay in power until the next City Council election shall be designated by the Prime Minister. Is shall take-over the powers and functions of the City Government and assume the respective powers and functions hereby vested in the City Council and the City Council and the City Cabinet. The Mayor of the City under the Provisional Governmént thereof shall exercise the powers and functions herein given to the office of the Mayor.
3) The Provisional Government:
(a) shall designate sub–City and Kebele Provisional Government;
(b) shall effect sub-City and Kebele delimitations in accordance with this Charter;
(c) shall reorganize the administrative offices of the City Government as well as reassign, hire and dismiss employees in conformity with the organizational structure it is to approve;
(d) may establish during the transition period City as well as sub-City and Kebele Advisory Councils, comprising of inidividuals nominated by respective residents and different sections of society, in order to enhance the organized participation of residents in development, building of democracy and service delivery as well as to help render decisions in the interest of residents; subject to such details thereof as it shall subsequently set out.
4) The Provisional Government of the City shall reassign, train and may, where necessary, discahrge incumbent Executive Committee members. It shall assign, members of its leadership by way of appointment and transfer as well as discharge same as necessary.
5) The rights and obligations of such offices or juridical organs of the City Government as are supplanted or amalgamated by law as per the organizational structure to be approved by the Provisional City Government, shall be transferred to the corresponding offices or juridical organs thereby established or, where found appropriate, the matter shall be decided by the Provisional Government.

፮. የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር ለሽግግሩ ወቅት የሚያገለግል፣
   ሀ) የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ሕግ ያወጣል ፣ በመሆኑም የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕጎች ለሽግግር ወቅት በከተማው አስተዳደር ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም ፤
   ለ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፹፭ (እንደተሻሻለ) ተፈፃሚ የሚሆንበትን ዝርዝር ሁኔታ የሚወስን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ደንብ ያወጣል።
፯. የከተማው አስተዳደር እስካልተካቸው ድረስ በዚህ ቻርተር ውስጥ የተገለጹትን የማይቃረኑ በሥራ ላይ የነበሩ አዋጆች፣ ደንቦች ፣ ውሳኔዎች ፣ ትዕዛዞችና መመሪያዎች ተፈፃሚነት ይቀጥላል።
፰. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉና በዚህ ቻርተር መሠረት በከተማው ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መታየታቸው ይቀጥላል።
፱. አሁን በስራ ላይ ያሉት የከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንዲሁም የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች በዚህ ቻርተር አንቀፅ ፵፩ እና ፶ ለተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የተሰጡት የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል።

፷፯. የተሻሩ ህጎች

፩. የሕግ አወጣጡን ሥነሥርዓት ባልተከተለ አኳኋን የይዘት ለውጥ ተደርጎበት የታተመ በመሆኑ ፣ የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ ተሰርዞ በዚህ ቻርተር ተተክቷል።
፪. ከዚህ ቻርተር ጋር የሚቃረን ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ቻርተር በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፷፰. ቻርተሩ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ቻርተር ከጥር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

6) The Provisional City Government shall:
   (a) enact Civil Service Laws; Federal Civil Service Laws shall, therefor, be inapplicable to the City Government during the transition.
   (b) issue labour relations Regulations which set out, in detail, the circumstances under which the Labour relations Proclamation No. 42/1993 (as amended) is to be applied.
7) Proclamations, Regulation, decisions, orders and directives consistent with the provisions of this Charter shall remain in force so long as the City Government does not have them replaced.
8) Cases pending before Federal Courts and falling under the jurisdiction of the City Courts, in accordance with this Charter, shall continue to be adjudicated by the Federal Courts.
9) The Municipal First–Instance Court and Appellate Court as well as Social Courts in operation shall have the respective jurisdiction given to corresponding courts under Articles 41 and 50 hereinabove.

67. *Repealed Laws*

1) The Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 311/2003, having been published with its contents changed without following the Legislative Procedure, is hereby deleted and replaced by this Charter.
2) No law or customary practice inconsistent with this Charter shall be applicable in respect of matters provided for herein.

68. *Effective Date*

This Charter shall come into force as of the 23rd day of January, 2003.

*Date at Addis Ababa, this 24th day of July 2003.*

*GIRMA WOLDE GIORGIS*

*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*